ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 071 ኅዳር 11 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## "አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን ለመረዳትና በዘርፉ ለመራቀቅ ጉጉት ያለው ትውልድ መምጣቱ ትልቅ ተስፋ ነው"

- ሰሎሞን ካሳ
የቴክኖሎጂ ባለሙያ

ተስፋ ፈሩ

አዲስ አበባ፡- አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን ለመረዳትና በዘርፉ ለመራቀቅ ትልቅ ጉጉት ያለው አዲስ ትውልድ መምጣቱ ለነገዋ ኢትዮጵያ ትልቅ ተስፋ ነው ሲል ወጣቱ የቴክኖሎጂ ባለሙያ ሰለሞን ካሳ ገለጸ።

ወጣቱ የቴክኖሎጂ ባለሙያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ አርቴፊሻል ኢንተለጅንስን ለመረዳትና በዘርፉ ለመራቀቅ ትልቅ ጉጉት ያለው አዲስ ትውልድ መምጣቱ ለነገዋ ኢትዮጵያ ትልቅ ተስፋ ነው።

የወደፊቱ የሰው ልጅ ስልጣኔ ሂደት በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ላይ የሚመሰረት መሆኑን የገለጸው ሰለሞን፤ ሀገራችንን ሌላው አለም ከደረሰበት ደረጃ ጋር እኩል ለማድረግና ለችግሮቻችን የራሳችንን መፍትሄዎች ለማምጣት ትውልዱን በሰው ሰራሽ አስተውሎት ክህሎት የበለጸገ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቁሟል።

የዚህ ዘመን ልጆች እኛ ከነበርንበት ዘመን አንጻር የነቃ ንቃተ ህሊና ያላቸው ናቸው ያለው የቴክኖሎጂ ባለሙያው፣ "ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ፍሰት ከሁሉም አቅጣጫ የሚያገኙበት ዕድል በመኖሩ በዓለም ላይ የሚሆነውን ነገር ሲመለከቱ በሚፈጠርባቸው ቁጭት ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸውና ለሀገራቸው ከቴክኖሎጂው አንዳች ነገር ለማስገኘት ፍላጎትና ጉጉት ያድርባቸዋል" ብሏል።

እንደ ሀገርም እውቀት ላይ የተመሰረተ የቴክኖሎጂ ዕድገት የወደፊቱን ጊዜ እንደሚወስን በመረዳት በቁርጠኝነት በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ላይ ለመስራት እየተደረገ ያለው

"አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






## ከኦላፍ ሾልዝ ጋር የተደረገው ውይይት የኢትዮጵያና የጀርመንን ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክር ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከጀርመን ቻንስለር ኦላፍ ሾልዝ ጋር ያደረጉት ውይይት በሁለቱ ሀገራት ያለውን ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክር መሆኑን አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ ገለጹ።

ከኦላፍ ሾልዝ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አቶ መላኩ ታዬ

## በሀገሪቱ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲኖር እየተሠራ ነው

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ አብዛኞቹ አካባቢዎች አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እያገኙ ባለመሆኑ አገልግሎቱን አስተማማኝ ለማድረግ እየሠራን መሆኑን

በሀገሪቱ አስተማማኝ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ቋሚ ኮሚቴዎች ትብብራቸውን ሊያጠናክሩ ይገባል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን እና የሕግ የበላይነት እንዲከበር የሕዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤቶች የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች ትብብራቸውን ማጠናከር እንደሚገባቸው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ አሳሰቡ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከክልል ምክር ቤት የሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር ትናንት ምክክር እና የልምድ ልውውጥ ተካሂዷል፡፡

አቶ ታገሰ በውይይቱ መክፈቻ ላይ እንደተናገሩት፤ ሕግ አውጭው አካልና የፍትህ ዘርፉ ሥራዎቹ በሚፈለገው ፍጥነት እንዲሄዱ ትብብርን በማጠናከር መሥራት ይገባቸዋል፡፡

የፍትህ አካላት የለውጥ ሥራ ለሀገር ሰላም እና ለሕዝብ ደህንነት፣ የሕግ የበላይነትን ለማስከበርና ለልማት ሥራ ወሳኝ በመሆኑ ትግበራው በሚፈለገው ፍጥነት ሊቀጥል ይገባል፡፡ ትብብሩ በፍትህ ዘርፉ የሚተገበሩ የለውጥ ሥራዎች የተናበቡ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡

የዘርፉን አመራር እንዲሁም አፈጻጸምን ለማሻሻልም እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ የሕግ ማዕቀፎችን ለመፈተሽ ይረዳል፣ ለልማት ሥራ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ወሳኝ ነውም ብለዋል፡፡

በፍርድ ቤት አሠራር ውጤታማ ተግባር ለማከናወን፣ በዐቃቤ ሕግ የክስ አቀራረብና በፖሊስ የምርመራ እንዲሁም በማረሚያ ቤት የማረምና የማነጽ ሥራው ጥራት ያለው እንዲሆን ለማድረግ በሚሰራው ሥራ ውስጥ እጅግ ወሳኝ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ግብአትን ለማሟላት፣ በዘርፉ ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ለማዋል የተናበበ ሥራ ወሳኝ ነው ያሉት አቶ ታገሰ፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከክልሎች የፍትህ ተቋማት ጋር በጋራ በመስራት በፍትህ

የሕግ የበላይነትን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አቶ ታገሰ ጫፎ






# በማዕድን ዘርፉ በሩብ ዓመቱ የተሳካው የገቢ እቅድ 56 በመቶ ብቻ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከማዕድን ዘርፉ ይገኛል ተብሎ ከታቀደው አንጻር ማሳካት የተቻለው 56 ከመቶ ብቻ መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቴዮስ በተለይ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተገኘው ከ63 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ከእቅዱ አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙ 56 በመቶ ነው፡፡

በተለያዩ ኩባንያዎች የሚመረት አንድ ሺህ 245 ኪሎ ግራም ወርቅ ለውጪ ገበያ በማቅረብ 75 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እንደነበር አስታውሰው፤ ከኩባንያዎቹ የተገኘውን ከ719 በላይ ኪሎ ግራም ወርቅ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከ41 ሚሊዮን በላይ ዶላር ገቢ መገኘቱን አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪ ባህላዊ አምራቾች የተመረተ ከ202 ኪሎ ግራም በላይ ወርቅ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከ17 ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደተገኘ ጠቁመዋል።

አቶ ሚሊዮን እንዳስታወቁት፤ በባህላዊ አምራቾችና በተለያዩ ኩባንያዎች የተመረቱ ከ15 ሺህ ቶን በላይ የኢንዱስትሪ ማዕድናትን ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ 26 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ስምንት ሺህ 336 ቶን ኢንዱስትሪ ማዕድናት ለውጪ ገበያ ቀርበዋል፡፡



በሩብ ዓመቱ ከኢንዱስትሪ ማዕድናት ወጪ ንግድ አንድ ነጥብ 26 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን አመላክተዋል።

ሰባት ሺህ 359 ቶን ሊቲየም ማዕድን ለውጭ ገበያ በማቅረብ አንድ ነጥብ 56 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር መገኘቱን አስረድተዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ ከታንታለም ምርት አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 0 ነጥብ 69 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተገኝቷል ብለዋል፡፡

የዓለም አቀፍ የታንታለም መሸጫ ዋጋ መውረድን ለአፈፃፀሙ መቀነስ ምክንያት መሆኑን ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ የማዕድናት ገቢ አፈጻጸሙ ማነሱን አመላክተው፤ የፀጥታ ስጋት፣ የኮንትሮባንድ ንግድ እና ሕገ-ወጥ ግብይት፣ በኩባንያዎች በኩል በውጭ ምንዛሪ ዕጥረት የተነሳ የመለዋወጫ ዕቃዎች ዕጥረት መፈጠሩ ለወጪ ንግዱ ዋነኛ ተግዳሮት መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

ማዕድን በሚወጣባቸው አካባቢዎች የሚስተዋለውን የፀጥታ ችግር ለማስተካከል ከፀጥታ አካላትና ከክልል አመራሮች ጋር ውይይት ከመደረጉም በተጨማሪ በማዕድን ማምረቻ ቦታዎች የፀጥታ አካላትን የማስፈር ሥራ መከናወኑን ተናግረዋል፡፡

የኮንትሮባንድ ችግሮቹን ለመቅረፍ ከፍተኛ የፌዴራል አመራሮች የተካተቱበት ኮሚቴ ተዋቅሮ እየሰራ ይገኛል፤ ከፍተኛ አመራሮች ከክልል እስከ ወረዳ ያሉ አመራሮችን በአካል በማግኘት በሕጋዊ የማዕድናት ምርትና ግብይት ዙሪያ በመስክ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተከናውኗል ብለዋል፡፡

የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ደካማ ጎኖችን በማስተካከል በሁለተኛው ሩብ ዓመት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

በ2016 በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፍ ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት መታቀዱን የማዕድን ሚኒስቴር ማስታወቁ የሚታወስ ነው።



ዳጋቶ ኩንቤ

# ተቋማት አገልግሎቶቻቸውን ዲጂታሳይዝ አለማድረጋቸው ሀሰተኛ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ፈተና ሆኗል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ተቋማት አገልግሎቶቻቸው ዲጂታላይዝ አለማድረጋቸው ሀሰተኛ ሰነዶችን የማረጋገጥ ሂደት ላይ ክፍተት እየፈጠረ መሆኑን የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዳጋቶ ኩንቤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ተቋሙ የተለያዩ ሰነዶችን በማረጋገጥ የሚመዘግብ ሲሆን፤ አንዳንድ አካላት ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት በተቋሙ የተመዘገበ በማስመሰል መብቶች ላልተገባ አካል የሚተላለፍበት ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡

ሀሰተኛ ሰነድ የተቋሙ ዋነኛ ችግር ሲሆን ይህንን ለመፍታት አንዱ መፍትሄ ተቋሙ ዲጂታላይዝ ያደረጋቸው አገልግሎቶች ሌሎች ተቋማትም እንዲጠቀሙት በሲስተም ማስተሳሰር መሆኑን ገልጸው፤ በአሁኑ ሰአትም ሲስተሙን ከበርካታ ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

አቶ ዳጋቶ አንዳንድ አካላት አገልግሎት ለማግኘት ይዘው የሚመጧቸው የማንነት ማረጋገጫ ማስረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መረጃውን የሰጠው ተቋም ሙሉ በሙሉ አገልግሎቶቹን ዲጂታላይዝ ማድረግ ባለመቻሉ በቀላሉ የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንደሚያስቸግርና ከዚህ ጋር ተያይዞም በርካታ ክፍተቶች እንደሚፈጠሩ ገልጸዋል፡፡

ይህንን ችግር ለመቅረፍም በሀገሪቱ እንደዚህ ያሉ አገልግሎቶች የሚሰጡ ተቋማት አገልግሎታቸውን ዲጂታላይዝ ማድረግ ቢችሉ ሀሰተኛ ሰነድን በቀላሉ መለየትና ማረጋገጥ በማስቻል ችግሩን መፍታት እንደሚቻል ጠቅሰዋል፡፡


በአሁኑ ጊዜ ሀሰተኛ ሰነድን ለመከላከል ጠንካራ የሚባል የቁጥጥር ሥራ እየተሰራ ይገኛል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ እንደዚህ ያሉ ሥራ ላይ የሚሳተፉ አካላት ሲገኙም ወደ ህግ አካላት በማቅረብ ተጠያቂ እንዲሆኑ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በ2016 ሩብ አመትም በአዲስ አበባ ከተማ 462 የሚሆኑ ሀሰተኛ ሰነዶች የተያዙ ሲሆን አብዛኛዎቹ ሀሰተኛ ሰነዶች ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎቾ ናቸው ብለዋል፡፡ ይህንን ለመፍታትም ከአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ጋር ችግሩን መፍታት በሚቻልባቸው ጉዳቾ ላይ ውይይት መደረጉን ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡

በተያያዘም የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት በቀን ከ 6ሺ በላይ ተገልጋዮችን የሚስተናገድ ሲሆን የሚሰጡትን አገልግሎቶች ሁሉ ቀጠሮ አልባ ማድረግ መቻሉን አቶ ዳጋቶ ገልጸዋል፡፡

በ 2016 በመጀመሪያ ሩብ አመት አፈጻጸም 294ሺ የሚሆኑ ጉዳዮች ማረጋገጥና ከ400ሺ በላይ ተገልጋዮችን ማስተናገድ የተቻለ ሲሆን፤ በዚህም ከ680 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰብ መቻሉን አብራርተዋል፡፡

ዳይሬክተሩ በአሁኑ ጊዜ የሚሰጡ ሁሉም አገልግሎቶች በሲስተም የሚሰሩ ማድረግ መቻሉን ገልጸው፤ በቀጣይ ደግሞ ሰዎች ወደ ቢሮው በአካል መሄድ ሳይጠበቅባቸው አገልግሎት የሚያገኙበት በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥራ ለመስራት እየተሞከረ መሆኑን ተናግረዋል፡፡



# በክልሉ የኮሌራ ወረርሽኝ ከተከሰተባቸው 35 ወረዳዎች በ11ዱ መቆጣጠር ተችሏል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል የኮሌራ ወረርሽን ከተከሰተባቸው 35 ወረዳዎች ውስጥ በ11ዱ ወረዳዎች ወረርሽኙን ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር መቻሉን የክልሉ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አስታወቀ። በክልሉ በተከሰተው የኮሌራ ወረርሽኝ ሳቢያ 4 ሺህ 603 ሰዎች በበሽታው የተያዙ ሲሆን የ86 ሰዎች ህይወት አልፏል።

የአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ በላይ በዛብህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል ኮሌራ ወረርሽኝ ሀምሌ 7 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰተ ሲሆን፤ እስካሁንም 4 ሺህ 603 ሰዎች በበሽታው ተጠቅተዋል፤ ከ86 ሰዎች ደግሞ ሕይወታቸው አልፏል።

በክልሉ ወረርሽኙ በምእራብ ጎንደር በተለያዩ ወረዳዎች ከዛም አልፎ በባህር ዳር ዙሪያ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ደቡብ ጎንደር እንዲሁም በቅርቡ በሰሜን ወሎ ወረዳዎች በተለይም በራያ አላማጣ እና ኮረም ወረዳ ጨምሮ በ35 ወረዳዎች ላይ ተከስቷል።

ከነዚህም 35 ወረዳዎች ውስጥ 11 ወረዳዎችን ወረርሽኑን ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር ተችሏል። በቀሩት 24 ወረዳዎች ላይ በሽታውን ለመቆጣጠር ክትባት ከመስጠት ጀምሮ የተለያዩ የህክምና አገልግሎቶችን በመስጠት በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል።

በዚህም የጎንደር፣ ባህርዳር እና ደብረብርሀንን ጨምሮ በዘጠኝ ወረዳዎች 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ክትባት ማግኘታቸውን አቶ በላይ አስታውቀዋል።

በዚህ በሽታ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃ ቢሆንም 77 በመቶ የሚሆኑት ታማሚዎች ከ15 አመት ጀምሮ እስከ 44 እድሜ ክልል ያሉት ሰዎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

አቶ በላይ እንደገለጹት፤ የንጹህ ውሃ አቅርቦት በሚፈለገው ሁኔታ አለመኖር፣ የመጸዳጃ ቤት እጥረት እንዲሁም በክልሉ በተፈጠረው ግጭት ብዛት ያለው ተፈናቃይ እና ድርቅ መኖሩ ለወረርሽኙ መስፋፋት ምክንያት መሆናቸውን ገልጸዋል።

ለዚህም የንጹህ ውሃ መጠቀም፣ በመጠለያ እና በእምነት ቦታዎች ላይ ለበሽታው አጋላጭ ሁኔታዎችን እንዳይከሰቱ መጠንቀቅ ብሎም በሽታው እንደታየ ቀጥታ ወደ ጤና ተቋማት መሄድ ያስፈልጋል ሲሉ አስታውቀዋል።

ለዚህም ኢንስቲትዩቱ የራሱ ህክምና መስጫ ማእከልና ህክምናውን ከመስጠት ጀምሮ ምላሽ መስጫ ማእከል በማቋቋም ስለታማሚዎች እና የህክምና አገልግሎት ብሎም አስፈላጊ ድጋፎች በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎችን በመቀያየር እየተሰራ ነው።

የኮሌራ ወረርሽኝ ሁሉም በጋራ መስራት የሚያስፈልግ በመሆኑ ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል ያሉት አቶ በላይ በግብአት እና በክትባት ድጋፍ ላይ ትኩረት እንዲደረግ ጠይቀዋል።

ዜና

## ዩኒቨርሲቲዎቹ አዲስ ተማሪዎችን ተቀብለው ለማስተማር ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አዲስ ገቢ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር የሚያስፈልገውን የትምህርት ዝግጅትና የግብዓት አቀርቦት አጠናቅቀናል ሲሉ ገለጹ።

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳምጠው ዳርዛ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ወስደው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ነጥብ አምጥተው ወደ ዩኒቨርሲቲው የተመደቡ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅቱን አጠናቋል።

ለተማሪዎች የሚያስፈልጉ የዶርሚተሪ፣ የመመገቢያ ካፌና የህክምና አገልግሎት እንዲሁም የምግብ አቅርቦትና የመምህራን ምደባ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ብቻ ነው የሚቀረው ብለዋል።

የተማሪዎች ኅብረት፣ መምህራንና አስተዳደሩ፣ ማኅበረሰቡና የፀጥታ አካላት አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል፤ በተማሪዎች ላይ የሚደርስ እንግልትና መሰል ነገሮች እንዳይኖሩም ዝግጅት ተደርጓል ሲሉ አብራርተዋል።

ዶክተር ዳምጠው አይይዘውም፤ ለልዩ ፍላጎትና ለሴት ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ የማድረግ፣ የተለያዩ ሥልጠናዎች ለመስጠት የዝግጅት ሥራ እየተከናወነ ነው፤ ለትምህርታቸውም አመች የሆኑ የመማሪያና መኝታ ክፍሎች ዝግጁ ሆነዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ተማሪዎች ወደ ግቢው ሲመጡ የመጡበትን ዓላማ ለማሳካት ጠንክረው መስራት አለባቸው፤ ከሌሎች ወንድም እህቶቻቸው ጋር ተከባብረው መማር ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር ለዩኒቨርሲቲው የመደባቸውን ተማሪዎች ሲያሳውቀን ተቀብለን ለማስተማር የሚያስችል ቁመና ላይ እንገኛለን ሲሉ አመላክተዋል።

በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ፓል ፖት በበኩላቸው፤ ዩኒቨርሲቲው የ2016 አዲስ ምድብ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅቱን አጠናቋል ብለዋል።

የተማሪዎችን የመኖሪያ፣ የመመገቢያ፣ የህክምና የመሳሰሉ አገልግሎት መስጫዎችን ዝግጁ የማድረግ እና የምግብ አቅርቦት፣ የመምህራን የምደባና ሌሎች የዝግጅት ሥራዎች ተሠርተዋል ሲሉ አብራርተዋል።

ተማሪዎችን በሰላም ተቀብሎ ለማስተማር የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ፣ የተማሪዎች ኅብረት፣ የከተማው ነዋሪና የፀጥታ አካላት በቅንጅት እየሰሩ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ተማሪዎችን እንደ ወላጅ ተቀብሎ ለማስተናገድ መጠነ ሰፊ ሥራ ተሰርቷል፤ አሁን ተማሪዎችን እየጠበቅን ነው ብለዋል።

ለልዩ ፍላጎትና ለሴት ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው የገንዘብና የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ተማሪዎች ከፖለቲካ፣ ከዘረኝነትና ከብሔር አስተሳሰብ ነፃ በመሆን ከሌሎች እህት ወንድሞቻቸው ጋር በአንድነት ለመማር ተዘጋጅተው ሊመጡ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ብርሀነመስቀል ጠናም በተመሳሳይ፤ አዲስ ተማሪዎች ተቀብሎ ለማስተማር የሚያስፈልገውን ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲው የመማሪያ ክፍሎችን የማዘጋጀት፣ የአይ ሲቲ መሰረተ ልማቶችን የመዘርጋት ስራዎችን ሰርቶ ዝግጁ አድርጓል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በአጠቃላይ በጀቱ በሚፈቅደው ልክ ለተማሪዎች መማር ማስተማር የሚጠቅሙ ነገሮችን አዘጋጅቶ አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል እየጠበቀ ነው ብለዋል።

የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና መምህራን እውቀታቸውን ተጠቅመው ተማሪዎችን እንዲያበቁ እየተሰራ ነው ብለዋል፤ መምህራን ለተማሪዎች የተመደበውን የመማሪያ ጊዜ እንዳይሸራርፉ በኤሌክትሮኒክስ የታገዘ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ እየተሰራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

አዲስ ገቢ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማርና ለተማሪዎች የሚያስፈልጉ ማለትም የመማሪያ፣ የመኝታ፣ የመመገቢያ ክፍሎችን የማዘጋጀትና ለመማር ማስተማሩ የሚያስፈልጉ ግብቶችን የማሟላት ሥራ ተጠናቋል ሲሉም የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ አለምሸት ተሾመ ገልጸዋል።

ማህበረሰቡ አዲስ ተማሪዎችን የአደራ ልጆች ናቸው ብሎ የመቀበል ባህል ያለው በመሆኑ ለደህንነታቸው የሚያሰጋ ነገር የለም ሲሉም ገልጸዋል።

# ሙዚየሙ ቅርሶችን ከጥፋት ለመታደግ የሚያስችል መሆኑ ተገለጸ

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በግንባታ ላይ የሚገኘው የአማራ ህዝብ ሙዚየም ሲጠናቀቅ በክልሉ ለሚገኙ ቅርሶች የተሻለ ጥበቃ ለማድረግና ከጥፋቶች ለመታደግ የሚያስችል መሆኑን የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ዳይሬክተር አቶ ጋሻዬነህ አለፈ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በርካታ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች የሚገኙ ሲሆን ሙዚየሙ ቅርሶችን በአንድ ማዕከል በማሰባሰብ የተሻለ ጥበቃ ለማድረግና ከጥፋቶችን ለመታደግ ያስችላል፡፡

በ1 ነጥብ 186 ቢሊዮን ብር ወጪ በ2015 ዓ.ም ህዳር ወር ላይ ግንባታው የተጀመረው የአማራ ህዝብ ሙዚየም ፤አሁን ላይ ግንባታው 6 ነጥብ 98 በመቶ ተከናውኗል ተብሏል፡፡

ሙዚየሙ በባህር ዳር ከተማ ዓባይ ማዶ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ 15 ሺህ 600 ካ.ሜ ላይ ያረፈ ባለአራት ወለል ህንጻን ያካተተ ሲሆን በአማራ ህንጻ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ተቋራጭነት በአራት አመታት ውስጥ የሚከናወን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ቅርስ የአንድ ሀገር እና ማህበረሰብ ታሪክ ፣ባህል ፣ትውፊት ከዚህም ባለፈ ማንነት መገለጫ ስለሆነ ይህንን ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ ይገባል ያሉት አቶ ጋሻዬ፤ ለዚህም ቅርሶችን ከሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋ መጠበቅ ፣ ማልማትና መንከባከብ አለብን ብለዋል፡፡

ክልሉ እስካሁን ከ138 ሺህ በላይ የተመዘገቡ ቅርሶች ባለቤት ሲሆን ይህንን ሀብት መንከባከብ ብሎም ለህዝብ እይታ ምቹ በማድረግ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመው፤ ለዚህም አንዱ ተግባር የሙዚየም ግንባታ በመሆኑ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ይህም ቅርሶችን በማሰባሰብና በመመዝገብ ፣ ለጥናትና ምርምር ማዋል፣ ከመጥፋት ለመታደግና በዘመናዊ መንገድ በማስቀመጥ ለትውልድ በማስተላለፍ ረገድ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው አስታውቀዋል፡፡

ቅርሶቹን ከመንከባከብ እና ለትውልድ ከማስተላለፍ በተጨማሪ ሀገሪቱን ብሎም ክልሉን የቱሪስቶች መዳረሻ በማድረግና ለጎብኚ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የቱሪዝሙን ዘርፍ በማዘመን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይፈጥራል ብለዋል፡፡

ለዚህም ቢሮው ሙዚየሙ ያለውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በመረዳት ግንባታውን በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ በቅርበት የመከታተል ተግባር አጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ ጋሻዬ ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም ቅርሶቹ በሚገኙበት አካባቢ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች እና ባለድርሻ ለቅርሶቹ ጥበቃ እና እንክብካቤ በማድረግ ሀገሪቱ ከቱሪዝሙ ዘርፍ የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ የበኩሉን መወጣት አለበት ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡



# ኤጀንሲው

## አገልግሎቱን ለማሻሻል የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ሊያካሂድ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪዎች አገልግሎት ኤጀንሲ አገልግሎቱን ለማሻሻል የሚያስችለውን የኔትዎርክ መሰረተ ልማትና የባዮ ሜትሪክ መመዝገቢያ ፕሮጀክት ለማልማት ከከነራ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ጋር ስምምነት አደረገ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪዎች አገልግሎት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክትር ዮናስ አለማየሁ የስምምነት ሥነ ሥርዓቱ ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ኤጀንሲው በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም ከከተማው የህዝብ ፍላጎት አንፃር አዲስ አበባን የሚመጥን የመሰረተ ልማትና የሶፍትዌር አቅም የለውም፡፡ በዚህ ምክንያትም በተገልጋዮች ዘንድ ቅሬታ ይነሳል፡፡ ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትም ኤጀንሲው የባዮ ሜትሪክ መመዝገቢያና የኔትዎርክ መሰረተ ልማት ዝርጋታ ሊያካሂድ ነው፡፡

የኤጀንሲውን የቴክኖሎጂ አቅም ማሻሻል አስገዳጅ ሆኖ ተገኝቷል ያሉት አቶ ዮናስ፤ ኢጀንሲው አገልግሎቱን ለማዘመን ከ2015ዓ.ም ጀምሮ ሲሰራ መቆየቱን አውስተዋል፡፡ በተለይ ኤጀንሲው አገልግሎቱን ለማዘመንና ለማቀላጠፋ የኔትዎርክ መሰረተ ልማትና የባዮ ሜትሪክ መመዝገቢያ ፕሮጀክት ለማልማት ማስፈለጉን ገልጸዋል፡፡

በፕሮጀክቱ የዋና መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፎችን፣ ሁሉንም ክፍለ ከተሞች እንዲሁም የሁሉንም ወረዳ ጽህፈት ቤቶች የኔትዎርክ መሰረተ ልማቶችን የሚያሻሽል ተደርጎ የሚሰራ ይሆናል ብለዋል፡፡

ቴክኖሎጂው የኔትዎርክ ብልሽቶችን ያለ ባለሙያ ፍተሻ በቀላሉ መለየት የሚያስችል፣የሃርድዌር እቃዎችን በመቀነስ በሶፍትዌሮች የሚተካና ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፤ የዘርፉን የመልካም አስተዳደር ማነቆን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመፍታት የህብረተሰብን የአገልግሎት እርካታ ያሻሽላል ተብሎ እንደሚጠበቅም ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

አቶ ዮናስ አዲስ አበባን በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሽፋን የተሻለች ከተማ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት አገልግሎቱን ሙሉ በሙሉ ዲጂታል እንዲሆንና የሞባይል አገልግሎት ለመጀመር ይህ ፕሮጀክት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሰለሞን አማረ በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ ከዚህ በፊት የነበረውን የማይመች አሰራርን የሚቀይር፣ቀላል፣ ደህንነቱ የተጠበቀና አገልግሎትን በፍጥነት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑ ገልጸዋል፡፡

ኃላፊው ቴክኖሎጂው አለም አቀፍ ደረጃን (ስታንዳርድ) የሚያሟላ የዓይን ፣የፊት፣ የጣት አሻራ እንዲሁም የ"ላን" ኔትዎርክ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም ሲሆን አዲስ አበባን የኢትዮጵያ የስማርት ሲቲ ማዕከል ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት የሚያሳካና ምሳሌ የሚሆን ነው ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የሚሰራው በከነራ ኢንተርናሽናል ኩባንያ ሲሆን በ 4 ወራት ውስጥ ሥራው ተጠናቆ ወደ ሥራ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሕዝቦች ምክክር ለዘላቂ ሰላም!

ምክክር የችግሮች መፍቻ አንዱ ቁልፍ ነው፡፡ ሰዎች በርስ በርስ መስተጋብራቸው በመልካምም፣ በክፉም ሊወሳ የሚችል ሁነትና ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህ በመልካምም በክፉም የሚወሱ ሁነትና ሁኔታዎች ደግሞ የአሁናዊውን ብቻም ሳይሆን የቀጣይ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎችም መስተጋብሮቻቸው ላይ በአዎንታዊም፣ በአሉታዊም የሚገለጹና የሚንጸባረቁ ጉዳዮችን/አጀንዳዎችን ማሳረፋቸው አይቀሬ ነው፡፡

እነዚህ እንደየ ሁኔታው የሚከሰቱ አሉታዊም ሆኑ አዎንታዊ ጉዳዮች ታዲያ፤ ሰዎች በትናንት ታሪካቸው፣ በዛሬ ኑረታቸው አልያም በነገ የአብሮነት ጉዟቸው ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ በዚያው ልክ የሚገለጽ ነው፡፡ ምክንያቱም በመስተጋብሮቻቸው ወቅት የፈጠሯቸው አዎንታዊ ነገሮች በዛሬውም ሆነ በነገው የአብሮነት ጉዟቸው የትብብር አቅም የሚፈጥሩላቸውን ያህል፤ በመስተጋብሮቻቸው ምክንያት የፈጠሯቸው አሉታዊ ክስተቶች በዛሬው መገኘታቸውም ሆነ በነገ የአብሮነት ጉዟቸው ላይ ትልቅ እንቅፋት መሆናቸው አይቀሬ ነው፡፡

ለዚህም ነው የሰው ልጆች በትናንት ተረካቸው፤ በዛሬ ንግግራቸው፤ በነገ ትልምና ሕልማቸው መካከል ለሚታዩ ጉዳዮች ቁጭ ብለው ሲመክሩ፤ መልካሙን አጽንተው እኩይ የተባለውን አቅንተውና አጽድተው ዘመናትን ሲሻገሩ የኖሩት፡፡ ይሄ ደግሞ በግለሰቦች መካከል ለሚኖር መስተጋብር ብቻ የሚወሳ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም በቡድኖች፣ በማኅበረሰቦች፣ ብሎም በሀገር ደረጃ ሊኖርም፤ ሊገለጽም የሚችል ነው፡፡

በቤተሰብ ደረጃ የሚኖር ግንኙነት የሚፈጥረው መልካምም መጥፎም አጋጣሚ ደስታውም መከፋቱም የሚታየው በተመሳሳይ በሚኖር መስተጋብር ውስጥ ነው፡፡ እናም ቤተሰብ ውስጥ መጠራጠር፣ ቂምና ጥላቻ ብሎም ጠብና መለያየት እንዳይፈጠር፣ በሚያለያዩና በሚያቀያይሙ ጉዳዮች ላይ ቁጭ ብሎ በመነጋገር በይቅርታና እርቅ ይቋጫሉ፡፡ በፍቅርና ሰላም ይፈታሉ፡፡ ይሄ ሲሆን በመተማመን ላይ የተመሠረተ ቤተሰባዊ ኅብረት ይጸናል፡፡

በጉረቤትም፣ በአካባቢም በማኅበረሰብ ደረጃም የሚኖሩ መሰል መስተጋብሮች የጋራ ደስታንም፤ የጋራ ቂምና ቁርሾንም ሊፈጥሩ የሚችሉ እንደመሆናቸው፤ እነዚህ ቂምና ቁርሾዎች በዛሬው አኗኗራቸው፣ በነገው መንገዳቸው ላይ እንከን እንዳይሆን፤ በሽምግልናው መድረክ ቁጭ ብለው ይመክራሉ፡፡ ይወቃቀሱና ይቅር ተባብለው ይታረቃሉ፡፡ እናም በንጹህ ልብ፤ በፍጹም ኅብረት ዛሬያቸውን እየኖሩ፤ ወደ ነጋቸው በጠነከረ ኅብረት ይራመዳሉ፡፡

በአንድ ሀገር የሚኖሩ ሕዝቦችም እንዲሁ ናቸው፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የበዛ ማንነትን አቅፈው በያዙ ሀገራት ጉዳዩ ከፍ ብሎ የሚታይ ነው፡፡ ምክንያቱም በበዛ ማንነት ውስጥ የበዛ ባህልና ቋንቋ ብቻ ሳይሆን፤ የበዛ ፍላጎትና አለመግባባትም እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ይሄ የበዛ ፍላጎት ደግሞ የሚፈጥረው የጥቅም ግጭት፤ የፍላጎት አለመጣጣም፤ የሃሳብና ዕይታ ልዩነት ይኖራል፡፡

ኢትዮጵያውያን በኅብረት ቆመው የጻፏቸው ዘመን ተሻጋሪ የአብሮነት ድንቅ እሴቶች የመኖራቸውን ያህል፤ በበዛው ማንነት ውስጥ በሚፈጠሩ የፍላጎት መንገዶች ምክንያት እዚህም እዚያም የተከሰቱ አለመግባባቶችና ግጭቶች መኖራቸው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ሆኖም ከሚያቀያይሙት ይልቅ የሚያፋቅሩት፤ ከሚያለያዩት ይልቅ የሚያስተሳስሩት ጉዳዮች ገዝፈውና ጠንክረው በመገለጣቸው እነዚህ ጥቃቅን የቅያሜ አጀንዳዎች ከአብሮነት ሰገነታቸው ሳያወርዱ ዛሬ ላይ አድርሰዋቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ጥቃቅን ችግሮች በየጊዜውና በየዘመኑ እየታዩና እየተለዩ እልባት ስላልተሰጣቸው ብሎም እየተመከረባቸው ሁሉም ድርሻውን ወስዶ በይቅርታና እርቅ ባለመቋጨታቸው፤ ትልሹ ትልቅ እየሆነ በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬን፣ ቂምና ቁርሾን እያረገዘ ጉዳት አስከትሏል፡፡

ይሄ ደግሞ የሕዝቦችን አብሮነት፣ የሀገርን ሁለንተናዊ ከፍታና ብልጽግና በማይፈልጉ አካላት እየተጠለፈ በሕዝቦች መካከል የበለጠ የመጠራጠር ብቻ ሳይሆን የተበዳይነትና የበቀልተኝነት መንፈስ እንዲሰፍን እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ይሄም የበለጠ ችግሩን የሚያጎላ፤ ሕዝቦች የኖረ አብሮነትና ሕብር የደመቀው አንድነታቸው እንዲፈተን ያደርጋል፡፡

ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ሕዝብን እንደ መሸሸጊያ እየተጠቀሙ እኩይ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚውተረተሩ ኃይሎች እዚህም እዚያም ሰላምን ሲያደፈርሱ ማየት የተለመደው፡፡

ይሄ ችግር ደግሞ በጊዜ ካልተቋጨና ካልተገታ ለዜጎችም፣ ለሀገርም ትልቅ በሽታ ነው፡፡ ይሄ በሽታ ደግሞ ሕዝብን እንደ ሕዝብ፣ ሀገርንም እንደ ሀገር ሉዓላዊነትንም የሚገዳደር፤ አንድነትንና አብሮነትን የሚንድ ነው፡፡ ይሄ እንዳይሆንም ነው ዛሬ ላይ ዜጎች በችግሮቻቸው ላይ በግልጽ መክረው፤ በይቅርታና እርቅም ቋጭተው ከዛሬው ያለፈውን ነጋቸውን ብሩህ እንዲያደርጉ ለማስቻል ሀገራዊ ምክክር እንዲደረግ መንገዱ የተጀመረው፡፡

ይሄ ሀገራዊ ምክክር ደግሞ የተወሰኑ ቡድኖች አልያም የተወሰኑ ኃይሎች ብቻ ተገናኝተው የሚመክሩበት፤ በብዙሃኑ ፈንታ የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት የሚያስፈጽሙበት አይደለም፡፡ ይልቁንም ገለልተኛ ተቋም ተቋቁሞ ዜጎች ያለ ልዩነት የሚሳተፉበት፤ ያለ ተጽዕኖ ሃሳባቸውን የሚያራምዱበት፤ ያለ መሸማቀቅ ለይቅርታና እርቅ ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት፤ ይሄንኑም የሚያደርጉበት ነው፡፡

ይሄን እውን ለማድረግም የሕዝቦች መድረክ እየተዘጋጁ ሕዝቦች በጋራ እንዲወያዩ፤ ችግሮቻቸውን፣ ስሜቶቻቸውን፣ ቅሬታና መነዳታቸውን ብቻ ሳይሆን፤ ከዚህ ችግር የመውጫ መንገዳቸውን አንስተው እንዲወያዩ እየተደረገ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ እንደ ሀገር የገጠመንን ችግር ለመሻገር የሚያስችል ብቻ ሳይሆን፤ በቀጣይም የሚገጥሙንና ሊገጥሙን የሚችሉ እክሎችን በጽናት ማለፍ የሚያስችል አቅም ስለሆነ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሀገር በቀል የፈጠራ ሥራዎችን መደገፍ ለተሻለች ሀገር ግንባታ

ሰሚራ በርሀ

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ ከ50 አመት በላይ ያስቆጠረ ታሪክ ነው፡፡ ጊዜው በ1960 ዓ.ም ሲሆን በንጉሠ ነገሥት አጼ ኃይለሥላሴ የንግሥና ዘመን ላይ የሆነ ነው፡፡ በወቅቱ የተለያዩ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃና የኮሌጅ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ለተሻለ ትምህርት ወደ ተለያዩ የውጭ ሀገራት የሚላኩበት ጊዜ ነበር፡፡

ወደ ውጭ የተላኩ ተማሪዎችም ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ ሀገራቸው በመመለስ በተለያዩ ኃላፊነቶች ላይ ተሰማርተው ያገለግላሉ፡፡ በጊዜው ወደ ውጭ ሀገር ሄደው በኤሌክትሪካል ምህንድስና ትምህርት ተከታትሎ የመጣው የ25 አመት ወጣት ኢንጅነር ተረፈ ራስወርቅ ተጠቃሽ ነው።

ወጣቱ ኢንጅነር እንደመጣ፤ በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ቦርድ በሚባለው በአሁኑ ቴሌ- ኮም ተቋም ውስጥ የትራንስሚሽንና የረጅም ርቀት ስርጭት የሥራ ክፍል ውስጥ ተመድቦ መሥራት ይጀምራል፡፡

በጊዜው ፋክስ ባለመኖሩ የተለያዩ የመልዕክት ልውውጦች የሚደረጉት በቴሌግራፍ ነበር፡፡ እነዚህ የቴሌግራፍ መልዕክቶች የሚደረጉት በላቲን ፊደል ነበር፡፡ ወጣቱ ኢንጅነርም ሥራውን ከጀመረ በኋላ የራሷ ቋንቋ ያላት የራሷ ፊደል ያላት ሀገር በላቲን ፊደል መጠቀሟ ልክ ሆኖ አላገኘውም ፡፡

ለምን የራሳችንን ፊደል አንጠቀምም ብሎ በጠየቀበት ጊዜ ያገኘው ምላሽ ቴሌፕሪንተሩ የተፈጠረው ለላቲን ፊደል ነው የሚለው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ፊደላት ብዙ ስለሆኑ መቼም የማይቻል ስለሆነ ይህንኑ ብንጠቀም ይሻላል የሚል ተስፋ አስቆራጭ ምላሽ ነበር የተሰጠው ፡፡

ወጣቱ ኢንጅነር ግን አይቻልም የሚለውን ምላሽ ተቀብሎ የሚቀመጥ አልሆነም፡፡ ከዚያ ይልቅ የኢትዮጵያ ፊደላትን የያዘ ቴሌፕሪንተርን ለመሥራት ፊደላቱ ላይ ልዩ ጥናት ማድረግ ጀመረ፡፡ የፊደላቱን ንድፍ በወረቀት ላይ አውጥቶ ሲጨርስ ይህንን ለሚሠራ ሲመንስ ለተባለ የጀርመን ኩባንያ ልኮ እንዲሠራ አደረገ፡፡

ከዚያም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የአማርኛ ቴሌፕሪንተር በኢትዮጵያዊው ኢንጅነር ተረፈ ራስወርቅ ተሠራ፡፡ ለሙከራ እንዲሆንም አራት ቴሌፕሪንተሮች ወደ ኢትዮጵያ ተሠርተው ሲመጡ ለስሪታቸው የኢትዮጵያ መንግሥት አንድም የገንዘብ ድጋፍ አላደረገም ነበር፡፡

ይህንን ጉዳይ ያለ ነገር አላነሳነውም ምክንያቱም ኢንጅነሩ መጀመሪያ ሃሳቡ በውስጡ ሲውጠነጠን፤ ከዚያም የእንስራው ጥያቄውን ሲያቀርብ የተቀበለው አልነበረም፡፡ እሠራዋለሁ ብሎ ሲነሳም ውጤቱ እስከሚወታቅ ድረስ የደገፈው ሰው አልነበረም ፡፡

ወጣቱ ኢንጅነር በወቅቱ ጥያቄው የላቲን ፊደልን በዚህ መልኩ መሥራት ከተቻለ ለምን አማርኛን አንችልም የሚል ነበር፡፡ የቴሌፕሪንተሩን በመሥራቱ የአማርኛ ቋንቋን ብቻ ሳይሆን ትግርኛ፣ ኦሮምኛ ሌሎች የሀገራችን ቋንቋዎች በፕሪንተሩ መጠቀም እንዲቻል አድርጓል፡፡

ኢንጅነር ተረፈ ራስወርቅ ለሠሩት ለዚህ ትልቅ የፈጠራ ውጤት ከንጉሠ ነገሥቱና ከጥቂት አካላት በስተቀር እውቅና የሰጣቸው አልነበረም፡፡ ያም ሆኖ ግን በይቻላል መንፈስ የሄዱበት መንገድ እስከዛሬ የችግሩ መፍትሄ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

ሀገር በቀል ለሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ውጤት እውቅና በመስጠት እና በማበረታታት በኩል የሌሎች ሀገራትን ልምድ ስንመለከት ጃፓን እና ቻይና ዜጎቻቸው ለሚያመጧቸው የፈጠራ ሥራዎች እውቅና ይሰጣሉ፣ ያበረታታሉ፣ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋሉ፡፡

ከማበረታታትም ባሻገር ዜጎቻቸውን ከልጅነታቸው ጀምሮ በዚህ ታንጸው እንዲያድጉ የተለያዩ የልህቀት ማዕከላትን ገንብተዋል፡፡ በዚህም ራሳቸውን በቴክኖሎጂም ሆነ በሌሎች ፈጠራዎች ያደጉና ምሳሌ መሆን የቻሉ ናቸው፡፡

ወጣቶች ከአካባቢያቸው ጋር ቶሎ የሚላመዱ እና በሃሳብም በጉልበትም ንቁ የሆኑ ናቸው፡፡ ለሀገር ትልቅ ሀብት ሲሆኑ የተለያዩ ችግሮችን መፍታት የሚችሉና የሀገራቸውን ቀጣይ ዕድልም ጭምር የመወሰን ሥልጣን አላቸው፡፡ ታዲያ እነዚህን የሀገር ሀብቶች የሚሰማሩበትን መንገድ መመርመር እና የራሳቸውን ዐሻራ እንዲያኖሩ ማድረግ ይገባል፡፡

> **የቴክኒክና ሙያ ልህቀት**
> ማዕከላትን መገንባትና ማጠናከር፣ በተለያዩ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚሠሩ የፈጠራ ሥራዎችና ጥናቶችን ወደ ትግበራ ማምጣት፣ ተማሪዎች የሚሠሩትን የፈጠራ ሥራ ተግባራዊ የሚደረጉበት ሥርዓት መዘርጋት ይገባል

በሀገራችን ያሉ በተለያዩ የፈጠራ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ወጣቶች፣ የሥራ ፈጣሪዎችና ባለሙያዎች የሚያነሱት ችግር የሥራ ፈጣሪዎችን ለመደገፍ እንደ ሀገር የሚበጀተው በጀት ዝቅተኛ መሆኑን ነው።

የሥራ ፈጣሪዎች በሃሳባቸው ያለውን ሥራ ወደ መሬት አውርደው ውጤታማና ችግር ፈቺ መሆኑን አረጋግጠው ወደ ገበያው ለማስገባት ሲጥሩ የገንዘብ እጥረት እያጋጠማቸው ስለመሆኑም በተጨማሪነት ያነሳሉ፡፡

ሀገር በቀል የሆኑ የፈጠራ ሥራዎችን ማበረታታት እና ውጤታማ እንዲሁ ማድረግ አለመቻል፤ ሀገር ከውጭ የምታስገባቸው ምርቶች እንዲጨምሩ፤ የራሷን አቅሞች በአግባቡ እንዳትጠቀም ተግዳሮት የሚሆን ነው። ይህ ደግሞ የማደግ ራእዩን ጭምር የሚፈታተን ነው ፡፡

መንግሥት በዚህ ረገድ በተለያዩ ጊዜያት እየሠራቸው ያሉ ሥራዎች የሚበረታቱ ቢሆንም አሁንም በቂ ነው የሚያስብል ደረጃ ላይ የደረሰ አይደለም። በዘርፉ ገና ብዙ መሥራት የሚጠይቅ ነው። በተለይም የወጣቶችን የፈጠራ አቅም በማጎልበት ረገድ የተቀናጀ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

ለወጣት የሥራ ፈጣሪዎች ወርክሾፖችን በተገቢው መንገድ ከማደራጀት ጀምሮ፤ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግን፤ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋትን፤ ከዛም ባለፈ ጉዳዩን ከሀገራዊ የልማት ፖሊሲዎች ጋር በማስተሳሰር ከፍ ያለ ትኩረት የሚያገኙበትን መንገድ መቀየስ ወሳኝ ነው፡፡

የቴክኒክና ሙያ ልህቀት ማዕከላትን መገንባትና ማጠናከር፣ በተለያዩ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚሠሩ የፈጠራ ሥራዎችና ጥናቶችን ወደ ትግበራ ማምጣት፣ ተማሪዎች የሚሠሩትን የፈጠራ ሥራ ተግባራዊ የሚደረጉበት ሥርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡

የፈጠራ ሥራ ለሚሠሩ ወጣቶች እውቅና መስጠት (ሀገራዊ የእውቅና ሥርዓት መዘርጋት) ማበረታታት እና ወጣቶች በቀጥታ ከኢንዱስትሪዎች ጋር የሚተሳሰሩበትን መንገድ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለነገ የማይባል ሥራ ዛሬ ላይ መሥራት ከጀመርን ነገዎቻችን በዛሬ የተሣሉ ብሩህ ስለመሆናቸው ደፍሮ መናገር ይቻላል !።

# የፍሎራይድ ውሃ

## የሚያክሙ ተንቀሳቃሽ ማሽኖች ወደ ሀገር ሊገቡ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ድርጅት የከርሰ ምድር የሚገኘውን ከፍተኛ የፍሎራይድ ችግርን ማከ ተንቀሳቃሽ ማሽኖችን ወደ ኢትዮጵያ ሊያስ መሰረቱን ቼክ ሪፐብሪክ ያደረገው አፒሞሶ ከድርጅቱ ጋር በጋራ ለመስራት ውይይት ማያ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የአፒሞሶ ስ.አር.ኦ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃ ሴስታክ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እ የአፒሞሶ በኢትዮጵያ በመሰማራት ንጹህ የመ ለማቅረብ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከአዲስ ፍሳሽ ባለስልጣን ጋር በጋራ ለመስራት የሚ ስምምነት ለማድረግ የቅድመ ዝግጅት ውይይት

በዚህም በኢትዮጵያ ያለው የከርሰ ከፍተኛ የሆነ ፍሎራይድ ይዘት ያለው በመሆኑ ማሽኖችን በመጠቀም ውሃን በማከም እንደሚያቀርብ ገልጿል። ይህም ለሆስፒታሎች ጣቢያዎች ባሉበት አካባቢዎች በቀላሉ ንጹ ውሃን ለማቅረብ እንደሚያግዝ አስረድተዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ አፒሞሶ የው ቴክኖሎጂዎችን ወደ ኢትዮጵያ በማስመጣ ለመሰማራት በሂደት ላይ ሲሆን፤ በቀጣይም ይኖራሉ። በዋናነት ውሃን በማከም የንፁህ አቅርቦትን ማሻሻል ፣የተሻሻለ የውሃ ምንጭ ማሳደግ፣ የሥራና የክህሎት ልማት እድሎችን ጨምሮ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ድርጅቱ ከያዛቸው ዓላማዎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።



አንቶኒን ሴስታክ

በኢትዮጵያ ውስጥ የውሃ እጥረት፣ ብክለትና በቂ የመሠረተ ልማት አለመሟላት ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸውን በመጠቆም ችግሮችን ለመቅረፍ አፒሞሶ ቴክኖሎጂ የውሃ ማከሚያ ማሽኖችን በመጠቀም የዘላቂ የውሃ አያያዝን ለማረጋገጥ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

እንደ አንቶኒን ማብራሪያ፤ በቀጣይም አፒሞሶ በኢትዮጵያ ተንቀሳቃሽ የውሃ ማጣሪያ ማሽኖችን መገጣጠምና ማምረት የሚችሉ ፋብሪካዎችን በኢትዮጵያ ያቋቁማል። እንዲሁም በኢትዮጵያ የአቅም ግንባታን ለማሳደግ ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በትብብር ይሰራል። በኢትዮጵያ የተገጣጠሙ የውሃ ማጣሪያ ማሽኖችን ለአፍሪካ ሀገራት በማከፋፈል ተጠቃሚነትን ለማሳደግም ይሰራል።

በጤና ሚኒስቴር የሳኒተሪ ኢንጅነር አንለይ ታዴ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አፒሞሶ ድርጅት ከፍተኛ የሆነ በከርሰ ምድር የሚገኘውን ፍሎራይድን ማከም የሚችል የተንቀሳቃሽ የውሃ ማሽኖች አሏቸው። በዚህም በጋራ ለመስራት በቅድመ ዝግጅት ዙሪያ ውይይት ተደርጓል። ኢትዮጵያ በሪፍት ቫሊ ውስጥ የምትገኝ በመሆኗና ከቮልካኖ ጋር በተገናኘ የከርሰ ምድር ውሃ ላይ ከፍተኛ የሆነ የፍሎራይድ ችግር አለ። ይህም ካልታከመ ለመጠጥነት አይውልም። በአዋሳና ወንጂ አካባቢ በአጥንት፣ በጥርስ መበስበስና የመጉበጥ የመሳሰሉ የጤና ችግሮችን ፈጥሯል።

በአዲስ አበባ የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ሲከናወን ከፍተኛ የሆነ የፍሎራድ መጠን ያጋጥማል ያሉት ኢንጅነሩ፤ ጤና ሚኒስቴር አዲስ አበባ ባሉ ሆስፒታሎች ካስቆፈራቸው አራት ጉድጓዶች ውስጥ በሁለቱ ከፍተኛ ፍሎራይድ አጋጥሟል ብለዋል።

በዓለም የጤና ድርጅት ስታንዳርድ መሰረት በሊትር 1ነጥብ 5 ሚሊ ግራም ፍሎራይድ መገኘት ያለበት ሲሆን፤ በሊትር እስከ ስድስት ሚሊ ሊትር ፍሎራድ ተገኝቷል። ይህን ለማከም ከአፒሞሶ ጋር ለመስራት በሂደት ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

# ከኦላፍ ሾልዝ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ከጀርመኑ መራሒ መንግሥት ኦላፍ ሾልዝ ጋር ያደረጉትን ምክክር በተመለከተ በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ሁለቱ መሪዎች በሁለትዮሽ፣ ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይተዋል። በምክክሩ ጀርመን በኢትዮጵያ የምትሰማራባቸው ልዩ ልዩ የኢንቨስተመንት አማራጮችን በጋራ ለመለየት ተችሏል።

የጀርመን ተቋማት በኢትዮጵያ በኢነርጂና በአፈር ማዳበሪያ ዘርፎች መሰማራት በሚችሉበት ጉዳዮች ዙሪያም ትኩረት አድርገው መወያየታቸውን የተናገሩት አምባሳደር ታዬ፤ በአጠቃላይ ውይይቱ በሁለቱ ሀገራት ያለውን በመከባበር ላይ የተመሰረት መልካም ግንኙነት ያስቀጠለና ይበልጥ የሚያጠናክር መሆኑን ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ኢትዮጵያ ያጋጠማትን የውስጥ ችግር ለመፍታት መንግሥት ያከናወናቸውን ዘርፈ ብዙ ተግባራት በተመለከተ ገለጻ ማድረጋቸውን ያስታወቁት አምባሳደሩ፤ በአሁኑ ወቅትም ሰላምን በዘላቂነት ለመገንባት እንደ ሀገር እየተከናወኑ የሚገኙ ተግባራትን ማመልከታቸውን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የውስጥ ግጭትን በውይይት በመፍታት ሰላምን ለማረጋገጥ የተኬደበትን ርቀት በተመለከተ ለቻንስለር ኦላፍ ሾልዝ ገለጻ ተደርጓል ያሉት አምባሳደሩ፤ በቀጣናው እና በሱዳን ያለውን ችግር ለመፍታት ኢትዮጵያ ያከናወነችውን ተግባርና እየተጫወተች የሚገኘውን ገንቢ ሚና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ማስታወቃቸውን አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ አስረድተዋል።

ለሱዳን ቀውስ ሰላማዊ እልባት ለመስጠት በሚደረገው ጥረት ኢትዮጵያ ልትጫወተው ስለምትችለው ገንቢ ሚናም መሪዎቹ አንስተው ሃሳብ መለዋወጣቸውንም ገልጸው፤ ከምጣኔ ሀብት እድገት ጋር በተያያዘ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) እና መራሔ መንግሥት ኦላፍ ሾልዝ እዳን በማቃለል እና ማሸጋሸግ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይም መምከራቸውን ገልጸዋል።

ውይይቱ በሁለቱ ሀገራት ያለውን በመከባበር ላይ የተመሰረተ መልካም ግንኙነት ያስቀጠለ መሆኑንም አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ ተናግረዋል።

# "አርቴፊሻል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ገልጾ፤ "ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በክረምት መርሀ ግብር በሰው ሰራሽ አስተውሎት ስልጠና የወሰዱ 21 የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምርቃት ላይ ተገኝተው ተማሪዎቹን ማበረታታቸው መንግሥታቸው ለዘርፉ ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ የሚያሳይ ነው" ብሏል።

"በርካታ ታዳጊዎች ቴክኒካል ነገር ውስጥ እየገቡ ችግር የሚፈቱ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ ሲሳተፉ እየተመለከትን ነው። ለአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ትልቅ ፍላጎትና ቴክኖሎጂን ቶሎ የመቀበል አቅም ያላቸው ታዳጊዎች በሁሉም አካላት መደገፍ አለባቸው።" ሲልም አክሏል።

በቀጣዩ ትውልድ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ሁሉም ተቋማትና ግለሰቦች ፊት አውራሪነት መጀመር አለበት ያለው አቶ ሰለሞን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በባንክ፣ በቴሌኮምና በንግድ ዘርፍ ባሉ የግል ተዋንያን ወይም በመንግሥት ተቋማት ዘንድ ሀገር መቀየር የሚል ትልቅ ሀብት አለ። በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ላይ የሚሰራው ሥራ ከውጭ ሀገራት በሚገኝ እግዛ ላይ ብቻ መንጠልጥ የለበትም ብሏል።

እዚሁ ሀገራችን ያለውን ሀብት በማንቀሳቀስ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሰለጠኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን ማፍራት እንደሚቻል የገለጹት አቶ ሰለሞን፤ አቅሙና ብቃቱ ያላቸው የሀገር ውስጥ ተቋማት ዘርፉን በሪሶርስ እንዲደግፉ ጥሪ አቅርቧል።

# በሀገሪቱ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የሚያገኙ አብዛኞቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች አስተማማኝ የሆነ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እያገኙ አይደለም፡፡ ይህ የሆነው ለረዥም ዓመታት የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ መስመሮችና ኔትዎርኮች ባለመሻሻላቸው ነው፡፡ ችግሩን ፈትቶ ለዜጎች አስተማማኝ የሆነ አገልግሎት ለመስጠትም በአሁኑ ወቅት ሰፊ ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ በሀገሪቱ አብዛኛው ክፍል በተለያዩ ጊዜያት የሚዋዥቅ፣ የሚቆራረጥ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ነው ያለው፤ ይህም የሆነበት ምክንያት በኤሌክትሪክ ገመዶች፣ ትራንስፎርመሮችና አጠቃላይ መሰረተ ልማቶች ላይ በሚደርስ ዝርፊያና ጉዳት ነው፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም የማሳደግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፤ የተሠራውንና እየተሠራ ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ ተጠቃሚው ተደራሽ እየሆነ ያለው ባልተሻሻሉ እንዲሁም በነባር የዝቅተኛና መካከለኛ መስመሮች መሆኑን ለአልግሎቱ ጥራት እክል እንደምክንያት አንስተዋል፡፡

ይህ መሆኑ ደግሞ አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎችን አስተማማኝ የሆነ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

አብዛኛው የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት የሚሰጡ መሰረተ ልማቶች ያረጁ በመሆናቸው የማህበረሰቡን ኤሌክትሪክ ፍላጎት ተደራሽ ለማድረግ መሸከም የሚችሉ አይደሉም ያሉት አቶ መላኩ፤ ችግሩን ለመፍታትና የማህበረሰቡን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት አሟልቶ አስተማማኝ የሆነ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ነባር መሰረተ ልማቶችን የማሻሻል ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በተሰራው ሰፊ ሥራ በመጀመሪያ ምዕራፍ ድሬዳዋ፣ ሀዋሳ፣ አዲስ አበባ እና ባህርዳርን ጨምሮ መቀሌ፣ አዳማ፣ ጅማ እና ደሴ እንዲሁም ሌሎች ከተሞች የኔትወርክ ዝርጋታና የመሰረተ ልማት የመልሶ ግንባታ ሥራ ተደርጎላቸዋል ብለዋል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት ችግሩን ለመፍታት በስድስት ተጨማሪ ከተሞች ማለትም በወላይታ ሶዶ፣ በሻሸመኔ፣ በደብረ ማርቆስ፣ በጎንደር፣ በሐረርና በመሳሰሉት ከተሞች የኔትወርክ ዝርጋታ የማሻሻልና መሰረተ ልማት የመልሶ ግንባታ ሥራ ተጀምረዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም 72 ከተሞችን የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማታችን የመልሶ ግንባታና የኔትወርክ ዝርጋታ ለማድረግ በጀት ተይዟል ብለዋል፡፡

የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶችን ሙሉ ለሙሉ ለማሻሻል ከፍተኛ የሆነ በጀት ይጠይቃል ያሉት አቶ መላኩ፤ የተቻለውን ሁሉ አድርጎ ችግሩን ለማቃለል ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

አቶ መላኩ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ያላገኙ በርካታ የሀገሪቱን ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ አማራጮችን እየተጠቀመ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህም ከዋና ዋና ከተሞች ኃይልን በመጥለፍ የገጠር ከተሞችን ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

# የሕግ የበላይነትን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ዘርፉ የሕዝብን ርካታ ማሟላት ይገባቸዋል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ በፍትህ ዘርፉ የተጀመሩት የለውጥ ሥራዎች በሚፈለገው ፍጥነት መሄድ እንዳለበትም ተናግረዋል፡፡

ከየክልሉ የተወከሉ የምክር ቤት አባላት የፍትህ አካላት የለውጥ ሥራ ከዚህ በፊት ያልተተገበረ መሆኑን አስታውሰው፤ አሁን መጀመሩና ሰፊ እቅድ ተይዞ ችግሮችን በመለየትና አቅጣጫ በማስቀመጥ እየተሰራ መሆኑ በበጎነት እንደሚታይና ተግባሩ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም አመልክተዋል፡፡

የሕዝብን ማኅበራዊ እሴት መሰረት ባደረገ መልኩ መስራት እንደሚገባ እና ትግበራው በፍርድ ቤቶች ላይ የነበረውን ጫና በመቀነስ የሕዝብ ርካታ ለመፍጠር እንደሚያስችልም ተወያዮቹ አመልክተዋል፡፡ ለሀገር ሰላም፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ሀገርን እንደሀገር ለማቆም ፍኖተ ካርታውን በስኬታማነት ተግባራዊ ማድረግ ይገባልም ብለዋል፡፡

በፍትሕ ሂደት ችግር የፍርድ ቤት ትእዛዝ የማያከብሩ አካላት ላይ ትዕዛዝ እንዲከበር ምክር ቤቱ ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባም ተነስቷል፡፡ ለፍርድ ቤቶች የበጀት ድጋፍ ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባም ተጠቁሟል፡፡

በውይይቱ የፍርድ ቤቶች ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ ካርታ አፈጻጸም ያጋጠሙ ችግሮች፣ የሚጠበቅ ውጤት ዙሪያ ጽሁፍ ቀርቧል፡፡ የፍትሕ ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ ካርታ አተገባበር እና ምክር ቤቶች ስለሚጠበቅባቸው ሚና ላይም ገለጻ ተደርጓል፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## አዲስ ዕይታ- የአፍሪካ ተማሪዎች የሰው ሠራሽ አስተውሎት ውድድር

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በአፍሪካ የመጀመሪያው የሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርተፊሻል ኢንተለጀንስ) የተማሪዎች ውድድር በቅርቡ በአብርሆት ቤተመጻሕፍት ተካሄዷል:: ውድድሩን አብርሆት ቤተመጻሕፍት አፍሪካ ቱ ሲሊከን ቫሊ ኤ2ኤስቪ (A2SV) ከተሰኘ ግብረ ሠናይ ድርጅት ጋር በመሆን ነው ያዘጋጀው:: በውድድሩ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከተለያዩ 47 የአፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ ተማሪዎች ተሳትፈዋል፤ ከተሳታፊዎቹ ውስጥ ስምንት ተወዳዳሪዎች ወደ መጨረሻው ዙር አልፈዋል::

ለፍጻሜ ውድድር የደረሱት ስምንቱ ተወዳዳሪዎች በሰው ሠራሽ አስተውሎት ዘርፍ ያበለጸጓቸውን ሥራዎች ይዘው ቀርበዋል:: የፈጠራ ሥራዎቹም በሕክምና፣ በትምህርት፣ በሳይንስና በምህንድስና ዘርፍ የበለጸጉ ሰው ሠራሽ ውጤቶች ናቸው፤ ከስምንቱ ደግሞ ሦስቱ አሸናፊ ሆነዋል:: ለፍጻሜ ውድድር ከደረሱት ከስምንቱ ተወዳዳሪዎች የተወሰኑትን ሥራዎች በዛሬው ሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችንን እንዳስሳለን::

ተማሪ ሂዝሚና ተሩዝ እና የቱኒዚያ ጓደኞቿ ለሕክምናው ዘርፍ አጋዥ የፕሮጀክት ሃሳብ ይዘው ቀርበዋል:: በሰው ሠራሽ አስተውሎት በመታገዝ ለሕክምናው ዘርፍ አጋዥ የሆነ የዌብሳይትና የሞባይል መተግበሪያ ነው ያበለጸጉት:: መተግበሪያው በሰው ሠራሽ አስተውሎት በመጠቀም በአእምሮ ሕክምና ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በመቸር ትምህርቱን በቀላሉ ለመስጠት ያስችላል:: ለመላው አፍሪካ እንዲሰራ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን፤ በተለይ የአእምሮ ሕክምናን የበለጠ ለማወቅና ለመረዳት ይጠቅማል::

ተማሪ ሂዝሚና እንደምትለው፤ ይህ መተግበሪያ ሰው ሠራሽ አስተውሎትን በመጠቀም ስለአእምሮ ሕክምና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ይጠቅማል:: ስለአእምሮ ሕክምና ማወቅ ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚያገለግል ሲሆን፣ በተለይ የሕክምና ተማሪዎች፣ ተመራማሪዎች እና በመስኩ የሚሰሩ ሙያተኞች የአእምሮ ሕክምናን በተመለከተ የሚኖሯቸውን ጥያቄዎች በሙሉ ለሰው ሠራሽ አስተውሎቱ በማቅረብ ተገቢውን ምላሽ የሚያገኙበት ነው::


ከዚህ በተጨማሪም ስለአእምሮ ሕመምና ስለሕክምናው ዓይነት በደንብ ለማወቅ የሚፈልጉ ሰዎች ማወቅ በሚፈልጉት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለሰው ሠራሽ አስተውሎቱ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ፈጣን ምላሽ ማግኘት ስለሚያስችላቸው በቀላሉ እንዲያውቁት እና በደንብ እንዲረዱት ያስችላቸዋል:: ይህ ደግሞ በተለይ የሕክምና ተማሪዎችን ጊዜና ወጪ በመቀነስ በቀላሉ የአእምሮ ሕክምና ሥራዎችን ለመሥራት ያስችላል ብላለች::

መተግበሪያው አሁን ሥራ ላይ መዋሉን የምትገልጸው ተማሪዋ፤ በተለይ በአእምሮ ሕክምና ላይ ለሚሰሩ ባለሙያዎች ፋይዳው ከፍተኛ ነው ብላለች:: በቀጣይም ከአፍሪካ በመሻገር ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው መተግበሪያ እንዲሆን እንደሚሰሩ ተናግራለች::

ተማሪ ኤመን ብሪጅ እና ጓደኞቹ በውድድሩ ለመሳተፍ ከአልጄሪያ ነው የመጡት:: በውድድሩ ለህጻናት መማሪያ የሚያገለግል የሞባይል መተግበሪያ ይዘው ቀርበዋል:: መተግበሪያው ህጻናት በወላጆቻቸው እየታገዙ ተረት፣ ታሪክ፣ የትኛውንም ዓይነት የሳይንሳዊ መጽሐፍ፣ ስለማንኛውም ጉዳይ እውቀት እንዲያገኙ የሚያስችል ነው:: ይህም መተግበሪያ ወላጆች ልጆቻቸው እድሜያቸው የሚመጥነውን ትምህርት መርጠው እንዲከታተሉ ለማድረግ ይረዳል::

ለህጻናት መማሪያ ተብለው የሚዘጋጁትን መጻሕፍትንም ሆነ ሌሎች አጋዥ ማስተማሪያዎችን መተግበሪያው ሰው ሠራሽ አስተውሎቱን ተጠቅሞ መምረጥና መለየት እንደሚያስችል የሚጠቁመው ተማሪ ኤመን፤ በተለይ በዚህ ዘመናዊው ዓለም አፍሪካዊያን የራሳችን የሚሉትን ሁሉ አብሯቸው እንዲቀጥል ለማድረግ ይረዳል ይላል:: ለምሳሌ ህጻናት የእንግሊዘኛ ቋንቋን ለመማር በመጽሐፍ፣ በስዕልና በድምጽ ያፈለጉትን እንዲያውቁ ለማድረግ እንዲሁም ወላጆች በልጆቹ እድሜ መሠረት ለእነሱ የሚስማማቸውን ዓይነት ትምህርት እንዲያገኙ መምረጥ እንደሚያስችላቸው





**በውድድሩ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ47 የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ ተማሪዎች ተሳትፈዋል**

ይጠቁማል::

በአልጄሪያ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ለተማሪዎች የሚሰጠው ከአምስት ዓመት እድሜ ጀምሮ መሆኑን ጠቅሶ፤ "የትኛው ትክክለኛ ነው? የትኛው ደግሞ ትክክለኛ አይደለም?" የሚለው በወላጆች ተመርጦ እንዲማሩ ለማድረግ እንደሚጠቅም አስታውቋል:: አሁን የሰሩት ሞባይል መተግበሪያዎችን መሆኑን አስመልክቶ፣ በቀጣይ የድረገጽ መተግበሪያና ሌሎች ተጨማሪ እሴቶችን በማከል ለመላው አፍሪካ ተደራሽ የመሆን እቅድ እንዳላቸውም ተናግሯል::

ተማሪ አሴር ኃይሉ እና ጓደኞቹ ኢትዮጵያውያውን ተወዳዳሪዎች፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሶፍት ዌር ተማሪዎች ናቸው:: ‹‹ዘ-አርትቴክቸር›› የተሰኘ ዌብ ሳይትና የሞባይል መተግበሪያ ይዘው ቀርበዋል::

እነ ተማሪ አሴር የሰሩት መተግበሪያ አርክቴክቸሮች መሥራት የሚፈልጉትን ነገር ለሰው ሠራሽ አስተውሎቱ በሚሰጡት ጊዜ ቴክኖሎጂው የሚፈልጓቸውን ዲዛይኖች (ለመነሻ ሃሳብ የሚጠቅሙ) ሰብስቦ ያመጣላቸዋል:: በተጨማሪ መተግበሪያው ላይ ባለሙያዎች ገብተው ሃሳባቸውን እና ሥራቸውን በማጋራት እርስበርስ እንዲወያዩና ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ የሚያደርግ ነው:: ዲዛይኖቻቸውን መተግበሪያ ላይ በመለጠፍ እንዲሸጡም ያስችላል::

አርክቴክቸሮች አንድን ሥራ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ፕላትፎርም እንዳለውም ጠቅሶ፣ ለምሳሌ ሁለት አርክቴክቸሮች አንድ ሥራ በጋራ የሚሰሩ ከሆነ በፕላትፎርሙ እየተነጋገሩ ሁለቱም በእኩል ጊዜ ሥራቸውን መሥራት እንደሚያስችለው ተማሪ አሴር ይጠቁማል::

ብዙ ጊዜ አርክቴክሮች ሥራቸውን ሲሰሩ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ተደጋጋሚ በሆነ ሥራ ላይ መሆኑን የሚገልፀው ተማሪ አሴር፤ ይህ መተግበሪያ አርክቴክቸሮች ሥራቸውን ሲሰሩ እንዳይሰላቹ እንደሚያደርጋቸው ይናገራል:: መተግበሪያው ለአርክቴክቸሮች መነሳሳትን የሚፈጥር እና የተለያዩ ዲዛይኖችን ፈጥሮ የሚያቀርብ ሞዴል እንዳለው አመላክቷል ::

"ይህንን ሥራ የሰራነው አርክቴክቸሮች ዘንድ በመሄድና ጥናት በማድረግም ነው" የሚለው ተማሪ አሴር፤ በቅርባቸው ያዩትን ችግር መነሻ በማድረግ ይህንን መተግበሪያ ለመሥራት እንደቻሉ ይገልፃል:: ይህ መተግበሪያ አሁን በኢትዮጵያ ላሉ አርክቴክቸሮች ብቻ እንደሚሰራ ጠቅሶ፣ በቀጣይ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ በማሳደግ እንደሚሰራ አስታውቋል::

ተማሪ አራርሳ ደረስ እና ጓደኞቹም ኢትዮጵያውያን ተወዳዳሪዎች ናቸው:: እነ ተማሪ አራርሳ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚያገለግል የዌብ ሳይት ፕላትፎርም ይዘው ቀርበዋል:: የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በሰው ሠራሽ አስተውሎቱ በመታገዝ መጽሐፍን መሠረት ያደረገ ጥያቄ የሚያቀርቡበትና ጥያቄውን መሠረት ያደረጉ ምላሾችን የሚያገኙበት ለተማሪዎች አጋዥ የሆነ መተግበሪያ ነው ያበለጸጉት::

ተማሪዎቹ በመተግበሪያው በመጠቀም ለሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ጥያቄ የሚያቀርቡበት ብቻ ሳይሆን፣ የሙከራ ፈተና መውሰድም ይችሉበታል:: በየሳምንቱ የሚዘጋጅ ውድድር ስላለ ተማሪዎች በአንዴ በዚህ ውድድር ላይ ይሳተፋሉ:: ከዚያም ውጤታቸው ስለሚቀመጥላቸው ራሳቸውን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በማነጻጸር ያሉበትን ደረጃ ለማወቅና ራሳቸውን ለማትጋት ይረዳቸዋል::

ተማሪው አጋዥ መጽሐፍ ካለው መጽሐፉን በመጫን ከመጽሐፉ ጥያቄዎች እንዲወጡ እያደረገ መጠቀም ያስችለዋል ሲል ገልጾ፣ ይህንን መተግበሪያ መጠቀም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ወደ ድረ ገጹ ገብቶ መጠቀም ይችላል ብሏል::

ተማሪ አራርሳ ስለድረ ገጹ አጠቃቀም ሲናገር እንዳለው፤ አንድ ተማሪ የፈለገውን መጽሐፍ ወይም የሚፈልገውን ርዕስ ጉዳይ ብቻ በመምረጥ በማንበብ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ጥያቄ ካለው ለሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ያቀርብለታል። ሰው ሠራሽ አስተውሎቱም ምላሽ ይሰጠዋል:: ከዚህ በተጨማሪ ምን ያህል እንዳነበበ (እንዳወቀ) ራሱን ለመፈተሽ ከፈለገም ሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ጥያቄ እንዲሰጠው በመጠየቅ መፈተን ይችላል::

ይህ መተግበሪያ ለተማሪዎች ብዙ ነገሮችን ያቀልልላቸዋል የሚለው ተማሪ አራርሳ፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎቱ በጣም ዘመናዊ መሆኑንና ተማሪዎች ማቅረብ የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች ብዙ ሳይለፉ በፍጥነት ለማቅረብ ያግዛቸዋል ይላል::

"አሁን ላይ ድረ ገጹን ማንኛውም ሰው የፈለገውን ዓይነት መጽሐፍ በመጫን መጠቀም ይችላል" የሚለው ተማሪ አራርሳ፤ በቀጣይም መተግበሪያውን በማሻሻል ብዙ ነገሮች በመጨመር በቀላሉ ለማንበብ፣ ለማጥናትና ለፈተና መዘጋጀት እንዲችሉ ለማድረግ እንሰራለን ብሏል::

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ተማሪዎች ተማሪ አማኑኤል አያሌውና ጓደኞቹ ‹‹አድ ማስተር›› የተሰኘ ለሥራ ቀጣሪዎች እና ተቀጣሪዎች የሚያገለግል የዌብ ሳይት መተግበሪያ በውድድሩ ይዘው ቀርበዋል:: ተማሪዎቹ ያበለጸጉት ይህ መተግበሪያ፤ ሥራ ቀጣሪዎች እና ተቀጣሪዎች የሰው ሠራሽ አስተውሎትን ተጠቅመው የሚፈልጉትን ለሥራ ብቁ የሆነ ሰው መለየት ያስችላል::

ለምሳሌ አንድ ቀጣሪ ድርጅት ሠራተኛ ፈልጎ ቅጥር ሲያወጣ ለዚያ የሥራ መደብ እስከ 300 ሰዎች ሊያመለክቱ ይቻላሉ:: ተማሪ አማኑኤል እንዳለው፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ሦስት መቶ ሰዎች ያቀረቡትን የሥራ ማስረጃ በሚገባ ከመረመረ በኋላ ከእርሱ ውስጥ ከተቀመጠው መስፈርት የሚያሟሉትን ለሥራው የሚመጥኑ ብቁ አመልካቾች በየደረጃቸው በማስቀመጥ እስከ 70 በመቶ ውጤት ያላቸውን በመምረጥ ማለፋቸውን ያመለክታል:: ሌላኛው ፕላትፎርም ደግሞ የሰው ሠራሽ አስተውሎቱን ተጠቅሞ የቃል ፈተና በመፈተን ከእነዚያ ውስጥ ለሥራው ብቁ የሆኑትን በመመረጥ በደረጃቸው ማስቀመጥ የሚያስችለው ነው::

ሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ለተቀጣሪ ሠራተኞችም እንዲሁ ሥራ ለመቀጠር ሲያመለክቱ ያቀረቡትን የትምህርት ማስረጃ በመመልከት "ይህንን እንደዚህ ብታሻሻሉት" የሚል ምክረ ሃሳብ እንደሚያቀርብም ነው ተማሪ አማኑኤል የገለጸው:: የተረሱ ሌሎች ነገሮች ካሉም እንደሚያስታወስ ይናገራል:: ይህም ለቀጣሪዎችም ሆነ ለተቀጣሪዎች ሥራዎችን በማቅለል በአጭር ጊዜ ውስጥ ሥራና ሠራተኛ ለማገናኘት ያስችላል ይላል::

መተግበሪያው ላይ ለቀጣሪ ድርጅቶች ዳሽ ቦርድ እንደሚኖረው ጠቅሶ፣ በዚህም የሚፈልጉትን መለጠፍ እንደሚችሉም ጠቁሟል:: በቀጣይ ሌሎች መካተት ያለባቸው ነገሮች ካሉም በመጨመርና በማስፋት የተሻለ ነገር ይዘው እንደሚቀርቡ ጠቁሟል::

የአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ዳይሬክተር ኢንጂነር ውባየው ማሞ በውድድሩ መክፈቻ ላይ እንዳሉት፤ በአብርሆት ቤተ መጻሕፍት የማንበብ ባሕልን ከማሳደግ ባሻገር ሀገሪቱ በሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ላይ የምትሠራውን ሥራ ለማሳለጥ ነው ውድድር እና ዓውደ ርዕዩ የተዘጋጀው።

በውድድሩ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ47 የአፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ ሦስት ሺህ 709 ተማሪዎች ተሳትፈዋል:: ውድድሩ በተለየ ሁኔታም ከ500 በላይ ዩኒቨርሲቲዎችን ያሳተፈ ሲሆን፣ ከተሳታፊዎቹ ውስጥ ስምንት ተወዳዳሪዎች ወደ መጨረሻውን ዙር ማለፍ ችለዋል::

"ውድድሩ በተለይ በሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ትልቅ ለውጥ ማምጣት የሚችል ነው" ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ተማሪዎቹ ያቀረቧቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶችም ችግር ፈቺ የሆኑና በአፍሪካ አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን ገልጸዋል::

ውድድሩ በአብርሆት ቤተ መጻሕፍት የተካሄደ ሲሆን፣ ቱኒዚያ፣ ናሚቢያ እና አልጄሪያ በቅድመ ተከተል ከ1 እስከ 3ኛ በመውጣት የ30 ሺህ ዶላር አሸናፊ መሆን ችለዋል::

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የስንዴ ምርት እና የኢትዮጵያ ጉዞ

**ምሕረት ሞገስ**



ኢትዮጵያ የቆላ መስኖ ስንዴ ማልማት የጀመረችው ከዘጠኝ ዓመት በፊት እንደ አውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር በ2013/14 አካባቢ ነበር:: በአንድ ሄክታር መሬት ላይ የተጀመረው የቆላ ስንዴ በ2018 ዓ.ም 50 ሺህ ሄክታር መድረሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ከአምስት ዓመት ወዲህ ደግሞ የቆላና የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት መስፋፋት በመጀመሩ፤ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በሌሎች ክልሎች ተስፋፍቶ ባለፈው የ2013/14 የምርት ዘመን በአጠቃላይ 404 ሺህ ሄክታር መሬት ለስንዴ ልማት ውሏል::

በቆላማ አካባቢዎች ስንዴን ለዛውም በመስኖ ማልማት፤ ለብዙ ኢትዮጵያውያን አርሶና አርብቶ አደሮች እጅግ እንግዳ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: አሁን ግን በሺዎች የሚቆጠሩ አምራቾች እየተሳተፉበት ይገኛሉ:: ይህን ተከትሎ በስንዴ ምርት ልማት ኢትዮጵያ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ቶን ስንዴ ምርት ልታገኝ እንደምትችል እየተገለጸ ይገኛል::

የግብርና ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተው፤ በየዓመቱ ከ30 በመቶ በላይ የስንዴ ፍጆታዋን ከውጭ የምታስገባው ኢትዮጵያ አጠቃላይ ፍላጎቷ 97 ሚሊዮን ኩንታል አካባቢ ነው:: እ.አ.አ በ2022 ግን ምንም ዓይነት ስንዴ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳላስገባች ተገልጿል::

የኢትዮጵያ የስንዴ ምርት ልማት የትኩረት አቅጣጫን ተከትሎ በተሠራው ሥራ ዘንድሮ በመኸር ምርት 112 ሚሊዮን ኩንታል፣ እንዲሁም በመስኖና በበጋ ስንዴ ምርት ደግሞ 52 ሚሊዮን ኩንታል ይገኛል ተብሎ ተተንብዮዋል:: በመሆኑም የተተነበየው የምርት መጠን ከሀገር ውስጥ ፍላጎት አንፃር ትርፍ ምርት ይገኛል ተብሎ የተገመተ ሲሆን፤ በትንሹ 32 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እንደሚቻል ተጠቁሟል።

በኢትዮጵያ የመስኖ ስንዴ ልማት በአሁኑ ወቅት በጥራትና በመጠን አድጎል፤ በዚህም የኢትዮጵያን ፍላጎት ማሟላት ብቻ ሳይሆን ወደ ውጪ እስከመላክ ተደርሷል ተብሏል:: ይህ በተለይ የሀገርን ገፅታ በመገንባት ደረጃ ትርጉሙ ላቅ ያለ ስለመሆኑም ይነገራል:: ይህንና አጠቃላይ የስንዴ ምርት ልማት የትኩረት አቅጣጫን በተመለከተ የኢኮኖሚ ምሁራን የተለያየ ሃሳብ ይሰነዝራሉ::

ሶስተኛ ዲግሪያቸውን በልማትና ኢኮኖሚክስ ላይ የሠሩት እና በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህሩ ሞላ ዓለማየሁ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ከዚህ በፊት ከአትክልት እና ፍራፍሬ ወጣ ተብሎ በመስኖ ሰብል ወደ ማምረት አይገባም ነበር:: በአብዛኛው በተለይ በመስኖ ስንዴ አይመረትም ነበር:: አሁን ግን በስፋት ወደ ጥራጥሬ ተገብቷል:: በተለይ ስንዴ በስፋት በመስኖ እየለማ ነው:: ይህ ደግሞ እጅግ የሚበረታታ ነው::

የበጋ ስንዴ በመስኖ የሚመረት ሲሆን፤ በክረምት ዝናብ ላይ ጥገኛ በመሆን ከሚመረተው ስንዴ የተሻለ ምርታማ ነው:: ምክንያቱ ደግሞ በበጋ በቂ ርጥበት ብቻ ሳይሆን በቂ ሙቀት ይገኛል:: ይህ የስንዴውን ምርታማነት ከፍ ያደርገዋል:: በሌላ በኩል ስንዴ በክረምት በሚመረትበት ወቅት ዝናብ ከሚፈለገው በላይ የሚሆንበት አጋጣሚ መኖሩን ጠቅሰው፤ በበጋ ግን የሰብሉን ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ፤ ውሃ ሲያስፈልግ ብቻ በመስኖ እንደሚሰጥ አስታውሰዋል:: ይህ ውሃ ሲበቃው እንዲቆም መደረጉም ምርቱን የተሻለ ያደርገዋል ብለዋል::

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የግብርና ማዘመንና ገጠር ልማት ፖሊሲ ጥናት ማዕከል አስተባባሪ ታደሰ ኩማ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚገልፁት፤ ስንዴ በስፋት መመረት አለበት ተብሎ ከበልግ እርሻ ባሻገር በጋ ላይም መሞከሩ የሚበረታታ ነው:: በዓመት አንድ ጊዜ ከማምረት ይልቅ ሶስት ጊዜ እንዲመረት መደረጉ ምርታማነት የሚጨምር በመሆኑ ሃሳቡ የሚናቅ አይደለም:: ከአንድ ጊዜ በላይ በብዙ ቦታ ላይ ስንዴውን በስፋት ማምረት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን ሀገር ጠግባ ከተትረፈረፈ ወደ ውጭም ለመላክ ይቻላል:: ለውጭ ገበያ መዋሉ ደግሞ ሌላው ጥቅም ነው::

በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም ደረጃ ያሉ የዱቄት ፋብሪካዎች በጣም ብዙ ናቸው:: የኢትዮጵያም የስንዴ ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ነው:: የፋብሪካዎቹ ዓመታዊ ፍላጎት እጅግ በጣም ብዙ ነው:: በኢትዮጵያ የፍላጎቱ መብዛት ስንዴ ላይ ጤነኛ ያልሆነ የገበያ ውድድር እንዲኖር አድርጓል:: ለምሳሌ ፋብሪካዎች ሲገዙ አንዱ 7ሺህ ቢሰጥ ሌላው ደግሞ ዓመቱን ሙሉ ቁጭ ብሎ ባዶ ከሚቀመጥ ብሎ 7ሺህ 500 ይሰጣል:: በእዚህ ጊዜ ዋጋው ሳይታሰብ እየናረ ይመጣል:: ስንዴ በስፋት መመረቱ ይህን ችግር ለማቃለል የሚረዳ መሆኑንም (ዶ/ር) ታደሰ ይናገራሉ::

በብዛት ስንዴ መመረቱን እጅግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዱት ሌላኛው የኢኮኖሚ ባለሙያው (ዶ/ር) ሞላ፤ በዓለም ላይ ስንዴ ታዋቂ ምግብ ነው:: አግሮ ኢኮሎጂን ታሳቢ አድርገው የወጡ ብዙ የምርምር ውጤቶች እና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች አሉ:: ያንን ለመጠቀም ስንዴ ምቹ በመሆኑ በስፋት ማምረት እና ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው ብለዋል::

ሀገሪቷ በምግብ ራሷን ለመቻል ምን ደረጃ ላይ ናት? የሚለውን በመመዘን በኩል ሰንዴ ከፍተኛውን ሚና እንደሚጫወትም (ዶ/ር) ሞላ ያብራራሉ:: አንዱ ሀገር የሚመረተው የምግብ ዓይነት ሌላ ሀገር ላይመረት ይችላል:: ለምሳሌ በፊት በኢትዮጵያ እንደውም በአጠቃላይ በአፍሪካ አፐል አይመረትም ነበር:: እነአውሮፓ ደግሞ በስፋት ያመርቱ ነበር:: የሀገሮችን የምግብ ዋስትና መጠን በአፐል እንስፈር ቢባል አይሆንም፤ ምክንያቱም በሁሉም ሀገር አይመረትም:: በተቃራኒው ስንዴ ግን በየትኛውም የዓለም አቅጣጫ ይመረታል ተብሎ ይታሰባል:: ስለዚህ በአብዛኛው በዓለም ደረጃ የሀገር ምርት የሚለካው በስንዴ መሆኑን አስታውሰው፤ ያለውን የእህል ምርት በሙሉ ወደ ስንዴ ተቀይሮ የሚሰላ መሆኑን ይናገራሉ::

የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናዋ ምን ደረጃ ላይ ነው? የሚለውን ለማስላት፤ የሚሠራው የስንዴ አቅርቦት እና ፍላጎት ተሰልቶ ነው:: የሚሰላበት መንገድም ኢትዮጵያ ያመረተችው በቆሎ፣ ሽንብራም ሆነ አብሽ ማንኛውም ምርት ወደ ስንዴ ይመነዘራል:: ሁሉም ስንዴ ቢሆን ምን ያህል ይሆናል? የሚለው ታስቦ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ያህል ስንዴ ያስፈልጋል? አሁን የተመረተው ስንት ይሆናል? በምግብ እህል ራሷ ችላለች አልቻለችም? ምን አላት? ምን የላትም? የሚለው ሙሉ ሂሳቡ ሲሰላ የሀገር ፍላጎት ምን ይመስላል የሚለውም ታክሎበት በመጨረሻም የምግብ ዋስትናዋ ተሠልቶ ይቀመጣል ይላሉ::

እንደ ዶ/ር ሞላ ሁሉ ዶ/ር ታደሰም በስፋት ስንዴ መመረቱን ቢደግፉም፤ አጀማመሩ ላይ ግን ጥያቄ አላቸው:: ‹‹አመራረቱ ምን ያህል ሳይንሳዊ እና ምርታማነትን የሚጨምር ነው?›› ለሚለው ጥያቄ ምላሽ መገኘት አለበት ይላሉ:: ሥራው ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መደገፍ እንዳለበት በማስታወስ፤ ምርታማነትን የሚጨምሩ መሬቶች በደንብ መታየት እና መለየት እንዳለባቸው አብራርተዋል:: በተጨማሪ የውሃ ፍላጎት በቂነቱን በተመለከተም በደንብ ሊታሰብበት እንደሚገባ ተናግረዋል::

ጅምሩ መልካም ቢሆንም አብዛኛዎቹ ነገሮች በጥናት ላይ የተመረኮዙና ሳይንሳዊነት ቢኖራቸው ጥሩ ነው በማለት ያብራራሉ:: ለምሳሌ ሁሉም አፈር ተመሳሳይ አይደለም፤ ልዩነት አለው:: የአየር ሁኔታውም መታየት አለበት፤ በየትኛው አካባቢ በየትኛው የአየር ሁኔታ የሚለው መለየት አለበት:: ስንዴም የራሱ ባህሪ አለው:: ሁሉም ተመሳሳይ አይደለም ፤ ይለያያል:: ስለዚህ የበጋ ስንዴ ማምረቻ ቦታዎች፣ አፈር እና አየራቸው ምን ያህል ምቹ ነው? የሚለውን ሳይንሳዊ ጥናት ተደርጎበት ሊከናወን ይገባል ባይ ናቸው::

መንግሥትም ባሳለፍነው ዓመት ክፍተቶቹ የትኛዎቹ ናቸው የሚለውን ለይቷል የሚል ተስፋ እንዳላቸው የተናገሩት (ዶ/ር)ታደሰ ፤ የነበረውን ገምግሞ ቀጣዩን የበለጠ ሳይንሳዊ አድርጎ መቀጠል እንዳለበት ይመክራሉ::

በሌላ በኩል በኢኮኖሚ ባለሙያው በዶ/ር ሞላ የተጠቀሰው፤ ለስንዴ ትኩረት መስጠቱ አንደኛ ቴክኖሎጂ በስፋት ስለሚገኝለት ምርታማነቱን ለማሳደግ ያመቻል:: ሁለተኛው በዓለም ላይ የስንዴ ተጠቃሚ ብዙ ነው:: ብዙ ሀገሮች ስንዴን ይገዛሉ፤ ሰንዴ በዓለም ተፈላጊ እና ገበያ የማያጣ ምርት በመሆኑ ገዢ ይጠፋል የሚል ስጋት የለም:: እነዚህ ምክንያቶች በራሳቸው በስፋት መመረቱ ጠቃሚ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው ይላሉ::

ብዙ ሀገሮች ስንዴ ላይ ይሰራሉ፤ ኢትዮጵያም ስንዴ ማምረቷ በሀገር ገፅታ ላይ የሚኖረው ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም የሚሉት (ዶ/ር) ሞላ ፤ የምግብ ዋስትናዋ የት ደረጃ ነው፤ የሚለው የሚታየው ያመረተችው ከስንዴ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ጠቅላላ ሕዝቧ በዓመት ከሚፈለገው በላይ ከሆነ በምግብ እህል ራሷን ችላለች የሚባል መሆኑንም አስረድተዋል::

ጤፍ በስፋት ተመርቶ ወደ ውጭ ለመላክ ቢሞከር ውጤት ላያመጣ ይችላል፤ ምክንያቱም ምርቱ በዓለም የሚታወቅ አይደለም:: ስንዴ ግን ታዋቂ ነው:: ለስንዴ በዓለም ደረጃ የተገነባ ገበያ አለ:: ስንዴ ከተመረተ ገበያ አይጠፋም፤ ምክንያቱም ዓለም የሚሸምተው የስንዴ ምርት ነው:: ስለዚህ የዓለምን የገበያ አቅም መጠቀም ይገባል ብለዋል::

ነገር ግን ሁልጊዜም የሁኔታዎች ትንታኔ መሠራት አለበት ያሉት (ዶ/ር) ሞላ ፤ በስንዴ ያለንበት ደረጃ ከሌሎች ጋር ሲወዳደር ምን ደረጃ ላይ ነን? ምን ያህል ስንዴ አለ? የሚለው በየጊዜው እየተገመገመ መሔድ መቻል አለበት ሲሉ፤ እርሳቸውም ጥናት ላይ መመርኮዝ እንደሚገባ ይጠቁማሉ::

በዓለም ላይ ፍፁም የሚባል ነገር የለም:: አሁን ባለው ሁኔታ ስንዴ የተሻለ ገበያ አለው:: ወደፊት የሚሆነው አይታወቅም:: ዋናው ዘመኑ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ያንን ማካካስ ይቻላል:: ስንዴ ሲመረት ሌሎች እየተተው በመሆኑ፤ እነሱ ሲቀሩ የሚካካሱበት እና በሌላ የሚተኩበት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት ያመለክታሉ:: እዚህ ላይ ከውጭ የሚገባው ሌላው ምርት ከስንዴ ከሚገኘው ገቢ ያነሰ ወጪን ወይም የስንዴው ገቢ የተሻለ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባሉ::

(ዶ/ር) ሞላ እንደተናገሩት፤ ሌላው አመራረቱ ላይ የቴክኖሎጂ ሽግግሩን በደንብ ማካሔድ ያስፈልጋል:: አመራረቱን በደንብ ማሳለጥ እና የተሻለ ማድረግ ሀገሪቷ የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋታል:: ከገፅታ ግንባታ አንፃር ከታየ እስከ አሁን ድረስ ሀገሪቷ የስንዴ እርጥባን ተቀባይ ነበረች:: አሁን በምግብ እህል ራሷን ችላለች ባይባልም፤ ወይም የሕዝቧ የምግብ ፍላጎት እና ምርቱ የተመጣጠነ ባይሆንም ስንዴ ወደ ውጭ መላክ መጀመሯ በራሱ ገፅታዋን ለመገንባት የሚኖረው ጠቀሜታ ቀላል አይደለም::

ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ለአንድ ምዕተ ዓመት በሚባል ደረጃ የስንዴ እርዳታ ተቀባይ የምትባል ሀገር ስንዴ በብዛት እና በጥራት፤ ዓለም በሚፈልገው መልኩ አምርታ ከስንዴ ላኪ ሀገራት ጋር ተቀላቀለች መባሉ በራሱ ትርጉሙ ቀላል አይደለም ይላሉ:: እንደውም የውጭ ባለሃብቶችም በሀገሪቷ ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሳተፉ የሚያደርግ እና የሚያነቃቃ ነው ብለዋል::

በሌላ በኩል ዶ/ር ታደሰ፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ ደረጃ ከስንዴ ጋር እኩል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የኢትዮጵያን የምግብ ፍላጎት ለማርካት በቆሎ ላይ ቢሠራ መልካም ነው የሚል እምነት አላቸው:: ምክንያቱም በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች እና የአየር ፀባይ መብቀል ይችላል:: ቴክኖሎጂው እና ልምዱም ብዙ ቦታ ላይ አለ:: ምርታማነቱም በቀላሉ እጥፍ መሆን የሚችል ነው:: የአፍሪካ ሀገሮች በቆሎ ተመጋቢዎች ናቸው፡ ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በመጨመር ከስንዴው ጎን ለጎን በስፋት በቆሎ ላይ መሠራት አለበት የሚል እምነት እንዳላቸው ይናገራሉ::

በምግብ እህል ራስን ለመቻል ከአሁን በኋላ ጤፍ መጠቀም አያዋጣም:: ነባር ባህል ብቻ ያዋጣል ብሎ መቀጠል ትክክል አይሆንም:: ከዚህ በኋላ ጤፍ ቅንጦት እንደሚሆን አያጠያይቅም:: ስለዚህ ለውጥ ያስፈልጋል፤ ለውጡ ምን ላይ መሆን እንዳለበት የመንግሥት የቤት ሥራ ነው:: ስኳር ድንችን የመሰለ በብዙ ሀገራት ለምግብነት የሚውለው የሥራ ሥር ምግብ መዘንጋት የለበትም:: የምግብ ይዘቱ እና ጤናማነቱ ከተመሰከረለት ስኳር ድንች በተጨማሪ ካሳቫ እና የእንሰት ውጤት ቆጮ የመሳሰሉትንም ማየት ይገባል:: ከነባር ታዋቂ ምግቦች ውጭ ሌሎቹንም ማሰብ የግድ መሆኑንም አመልክተዋል::

በአጠቃላይ እንደ የኢኮኖሚ ምሁራኑ እምነት የበጋ ስንዴ ላይ ትኩረት ተደርጎ መሠራቱ መልካም ነው:: ከገበያም ሆነ ከቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት አንፃር አዋጪነቱ አያጠራጥርም:: ከስንዴ ተረጂነት ወደ ስንዴ ላኪነት መሸጋገር የሀገርን ገፅታ ለመገንባት የሚኖረው ጠቀሜታም በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ነገር ግን ሳይንሳዊ ጥናት ላይ መመስረት ቢቻል የበለጠ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል አመላክተዋል::

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የአባቷ ልጅ

አስመረት ብስራት

ያደገችው ብዙ የቤተሰብ አባል የሚንጋጋበት ውስጥ ነው። ከስልሳ በላይ ሰዎች በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩበት ነው። እናትዋ የእንግሊዝ ሀገር ዜጋ ቢሆኑም ነጭ መሆናቸው እስኪረሳ ድረስ በሀበሻዊት ሴት ወግና ማዕረግ ቤታቸውን ያስተዳድሩ ነበር።

እናትነት፤ ሚስትነት ልዩ ስጦታቸው እስከሚመስል ድረስ ልጆቻቸውን ባሰማሩት መስመር ልክ ሲመሩና ለስኬት ሲያበቁ የኖሩ እናት ናቸው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርት ሆነውም በርካቶችን ለቁም ነገር አብቀተዋል። እኚህ እናት ወልደው ያሳደጓቸው ልጆች ምን ዓይነት ይሆኑ?

አባትየው ደግሞ ዶክተር ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔር ይባላሉ። ዶክተሩ በትግራይ ክልል በዓድዋ ከተማ አቅራቢያ ባለችው "አዲ-እስላም" የተሰኘች የገጠር መንደር ነው የተወለዱት፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በ1955 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከተቀበሉ በኋላ የማስትሬትና ዶክትሬት ዲግሬያቸውን ከዌልስ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል፡፡ ዶክተር ተወልደ በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሳይንስ ፋኩልቲ ዲን ሆነው አገልግለዋል፡፡ ከ1975 እስከ 1983 በነበረው ዘመን ደግሞ የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ሆነው ሰርተዋል፡፡

አስመራ በሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሻዕቢያ) እጅ ስትገባ ደግሞ ወደ አዲስ አበባ መጥተው የባህል ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ሆነው ሀገራቸውን አገልግለዋል፡፡ በኋላም ለብዙ ዓመታት በሚታወቁበት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተርነት አገልግለዋል፡፡

ዶክተር ተወልደ ከእንግሊዛዊት ባለቤታቸው ሱ ኤድዋርድስ ጋር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚያስተምሩበት ጊዜ ነበር የተገናኙት። ፍቅር የማያስተሳስረው የሰው ፍጥረት የለምና ዘር ቀለምን ሳይቆጥሩ ሰው መሆናቸውን ብቻ አስበልጠው ለወግ ማዕረግ በቁ። እነ ዶክተር ተወልደ ከአብራካቸው ከወጡት ሶስት ሴት ልጆች መካከል የመጀመሪያ ልጅ ሮማን ተወልደ ብርሃን ገብረ እግዚአብሔርን ለዛሬ የሴቶች አምድ እንግዳችን አድርገን ጋበዝናታል።

የመልካም ዘር ፍሬ ሲታይ ይለያልና ብዙ ሰዎችን የምታግዝ ለወጣቶች ተስፋ የሆነች ሴት እንደሆነች ይመሰክሩላታል። ያሰበቻትን ዳር ካላደረሰች አትቆምም የሚባልላት ይህች ሴት «በሕይወቴ ተምሳሌቴ እናቴ ናት፤ ቤት ውስጥ ሚስትም እናትም ናት። ውጭ ደግሞ ጐበዝና ጠንካራ መምህርት» ትለናለች። የሮማን እናት ሱ ኤድዋረድስ ለረዥም ዓመታት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያስተማሩ መምህርት ናቸው።

ከመምህርነት ሥራ በኋላም በበጎ አድራጎት ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። በጎ አድራጎት መስጫው ለገበሬዎች የተፈጥሮ ማዳበሪያ አሰራር በማሰልጠን ምርታማ ሆነው ኑሯቸው እንዲለወጥ የሚያደርግ ገብረሰናይ ተቋም ነበር። ከሥራ በተጨማሪ ቤታቸው ውስጥ የሚያደጉ ብዙ ልጆች በተለይ በክረምት ፒያኖ፤ ሥዕል፤ እጅ ሥራን በማሰልጠን ልጆቹ የተለያዩ ክህሎቶች እንዲኖራቸው በማድረግ እንዳሳደጓቸው ታስታውሳለች።

«ልጅ ሆነን ቤት ውስጥ ግማሽ ቀን ትምህርት ቤት ከሄድን በግማሹ ጊዜ የቤት ውስጥ ሥራ መሥራት ግዴታ ነበር።» የምትለው ሮማን «እናቴ የምታሳድጋቸውም ሆኑ የወለደችን ሶስት ልጆች በመካከላችን ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይፈጠርብን በአንድነት በፍቅር እንድናድግ ብዙ ስርታለች» ብላለች።

ወይዘሮ ሱ ኤድዋረድስ ትውልድ ሀገራቸውን እንግሊዝን ረስተው ፍፁም ኢትዮጵያዊት የምትመስል እናት፤ የባሏን ቤተሰቦች ተቀብለው በሀበሻ ወግ በመስተንግዶ የምታስደስት ሴት እንደነበሩ ታስታውሳለች። «ሁልጊዜ በእናቴ ሚዛን ስለካ ልክ እሆን ይሆን እያልኩ እራሴን እመዝናለሁ» የምትለው ሮማን በምንም ነገር አለመሰልቸትን ግን ሙሉ ለሙሉ ከእናቷ መውረሷን ታስረዳለች።

ወይዘሮ ሱ ኤድዋረድስ እግሊዛዊነታቸውን ፍጹም ትተው ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ኖረውና ኢትዮጵያዊ ሆነው ነው የኖሩት፡፡ ከዚህ ዓለም ሲለዩም «ሀገሬ ኢትዮጵያ ነች፤ እዚሁ ቅበሩኝ» ብለው በኑዛዜያቸው መሠረት እዚሁ ኢትዮጵያ ነው የተቀበሩት፡፡

ሮማን ቤተሰባቸው ውስጥ ወደ ስልሳ የሚጠጉ ልጆች አብረው ማደጋቸውን ታስታውሳለች። በዝምድናም ይሆን በሌላ በአጋጣሚ ወደ ቤተሰባቸው የመጣ ሰው ሁሉ ከልጆቻቸው እኩል በማሳደግ ለወግ ማዕረግ ማብቃታቸውን ትናገራለች። «ልጅ ሆነን አታ የሚባሉ ሞግዚት ነበሩን፤ እስካሁንም አሉ። ወደ እኛ ቤት ሲመጡ ሁለት ልጆቻቸውን ይዘው ነበር የመጡት። አታ እንደ ሁለተኛ እናት ቤቱን ያስተዳድሩ የነበረ ሲሆን ልጆቻቸውም ከእኛ እኩል ተምረው አሁን ትልቅ ደረጃ ደርሰዋል» ትላለች ሮማን በትዝታ ወደ ልጅነት ቤታቸው ተጉዛ።

**«ልጅ ሆነን ቤት ውስጥ ግማሽ ቀን ትምህርት ቤት ከሄድን በግማሹ ጊዜ የቤት ውስጥ ሥራ መሥራት ግዴታ ነበር።»**



የዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት በአዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ የተወለደችው ሮማን እስከ አስራ አንደኛ ዓመቷ ድረስ አዲስ አበባ ሕዝባዊ ሠራዊትና ምስካየ ኅዙናን የተባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተምራለች። በአስራ አንድ ዓመቷ አባቷ ዶክተር ተወልደ የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ሆነው በመሾማቸው የተነሳ ወደ አስመራ ከተማ ከቤተሰቦቿ ጋር በመሄድ እስከ አስራ አንደኛ ክፍል አስመራ ተማረች። ከዛ በአስመራ በነበረው ሰላም መደፍረስ የተነሳ ኢህአዴግ ከመግባቱ ከአንደ ዓመት በፊት አዲስ አበባ በመምጣት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተናን ወሰደች።

«ከሁለት የተማሩ ወላጆች መወለዴ ትምህርቴ ላይ ትኩረት እንድሰጥ አድርጎኛል» የምትለው ሮማን ማትሪክን በጥሩ ውጤት በማለፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪያዋን ያዘች። ከዛም ብዙም ሳትቆይ ወደ እናቷ የትውልድ ሀገር እንግሊዝ ሀገር ሄደች።

ሮማን በተማረ ቤተሰብ ውስጥ ማደጓ በትምህርት ውጤታማ እንድትሆን ከማድረጉ ባሻገር ለመጻሕፍት ልዩ ትኩረት እንድትሰጥ፤ ከብዙ ሰዎች ጋር መሆንና ማህበራዊ ሕይወት የሚያስደስታት፤ እና ምንም ዓይነት ነገር ቢሆን ጫፍ ሳታደርስ እንዳታቆም እንዳደረጋት ትናገራለች።

በእንግሊዝ ሀገር ቆይታዋ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ማስተርስ ያዘች። ከዛ በኋላ ለምትወደው የመጽሐፍ ድርሰትና ሕትመት ሥራ እንዲያግዛት አርትኦት ተማረች። በመቀጠል ሴክሬታሪያል ሳይንስ፤ የኮምፒውተር ኮርሶች የተለያዩ ትምህርቶችን በመማር ካላት የሕይወት ልምድ ጋር ሁሉን ሞካሪ በሁሉም ዘርፍ የበቃች ባለሙያ እንድትሆን አድርጓታል።

ከትምህርት በኋላ በእንግሊዝ ሀገር በፀሐፊነት፤ በጉዳይ አስፈፃሚነትና በተለያዩ የአስተዳደር ሥራዎች ላይ ተሰማርታ በሀገረ እንግሊዝ መቆየቷን ታስታውሳለች።

ወደ ኢትዮጵያ ጠቅልላ ከገባች አስር ዓመታት ሆኗታል። ወደ ትውልድ ሀገሯ ለመኖር ወስና ከመጣች በኋላ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ በመሆን፤ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ የበላይ ኃላፊ በመሆን ኮቪድ ወረርሽኝ በዓለማችን ላይ እስኪከሰት ድረስ አገልግላለች።

«በኮቪድ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ሥራ በመተው የተወሰኑ የግጥም መጻሕፍቶችን፤ የሕፃናት መጻሕፍትን መጻፍ፤ ግጥሞች በእንግሊዝኛ ቋንቋ በመጻፍ አሳተሜአለሁ» የምትለው ሮማን ለሶስት ዓመታት ያህል ከራሷ መጻሕፍቶች በተጨማሪ የሌሎች ደራሲያንን መጻሕፍት የማሳተምና የማከፋፈል ሥራዎችን ሰርታለች።

የነፍሷ ጥሪ የሆነውን የመጻሕፍት ጉዳይ ከግብ ለማድረስ ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጋ ትታ ሙሉ ለሙሉ መጻሕፍትን ወደ ማሳተም፤ ወጣት ደራሲዎች የጻፏቸውን ጥሩ ይዘት ያላቸውን መጻሕፍቶች ማሳተምና ማከፋፈል ሥራን መሥራት ላይ ሙሉ ትኩረቷን አደረገች።

ከዚህ በተጨማሪ አሁን የሴቶች ደህንነትና ሰላም ኢንስቲቱዩት የተባለ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ እየሰራች ትገኛለች። «ድርጅቱ ጡረታ በወጡ አምባሳደሮች የተቋቋመ ሲሆን ሴቶች ሰላምና ደህንነት የሚጠበቅበትን አማራጮች ለማሳየትና ለማስጠበቅ የሚሰራ ድርጅት ነው» የምትለው «ሮማን በሙያዬ ሀገሬ የምትፈልገኝ ቦታ ሁሉ ተገኝቼ ብሰራ ደስታዬ ነው» ትለናለች።

«የሕይወት ፍልስፍናዬ አልሸነፍም ባይነት ነው የምትለው ሮማን ይህ ማለት በምንም ሁኔታ ውስጥ ስኬት ላይ እስከሚደረስ ድረስ መታገል የሕይወቴ አካል ነው» ብላለች። «ለእኔ ስኬት የሚደረስበት ሳይሆን የሚኬድበት መንገድ ነው» የምትለው ሮማን መንገዱ ላይ የሚገጥሙ እንቅፋቶችን እየተሻገሩ ማለፍ፤ መሰናክሎችን መዝለል፤ አለመቆም ሁሉ ስኬት ብላ እንደምትጠራው ታብራራለች። «እኔ ለኢትዮጵያ ሴቶች የምመክረው እናቶች ልጆቻቸውን ቁጭ ብለው ማሳደግ ታላቅ ሥራ ቢሆንም የተለያየ ሥራዎችን መሥራት እንደሚኖርባቸው ነው» ትላለች። ሴቶች ብዙ ክህሎት እያላቸው እጅና እግራቸውን አጣጥፈው መቀመጣቸው ሰብዓዊ መብቶቻቸውን ለማሰነጠቅ እንደፈቀዱ ያስቆጥራቸዋል ትላለች።

የገንዘብ አቅማቸውን ማሳደግ፤ በዕውቀት ራስን ማዳበር፤ የራስ መተማመናቸውን መጨመር ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለልጆቻቸው፤ ለቤተሰቦቻቸውና ለመላው ማህበረሰቡ ጠቀሜታው የላቀ ነው።

«ኢትዮጵያዊት ሴት ነኝ። የእናቴ ሀገር እንግሊዝ ሲሄድ እንኳን እንደ አንድ ስደተኛ ከመኖር ያለፈ የሀገር ዓይነት ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም ነበር» የምትለው ሮማን » ኢትዮጵያዊነት ሱስ እስከሚመስለኝ ድረስ እንግሊዛዊት ለመሆን ሞክሬ አላውቅም ነበር» ትለናለች። በእናቷ ትውልድ ሀገር ውስጥ ሆና ፍፁም በባይተዋርነት ስሜት ትሰቃይ እንደነበር ስታስታውስ።

ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ያለው የበዛ ወግ አጥባቂነት እንደሚገርማት የምትናገርው ሮማን ማህበራዊ ግንኙነት ጥሩ ቢሆኑም በተለይ የኢትዮጵያ ባህል ሴቶች ላይ በጣም የጠበቀ መሆኑ የወንዶች የበላይነት የጎላ መሆኑ ትንሽ ከበድ እንደሚል ታስረዳለች።

እንግሊዞች ግን ወግ አጥባቂ ቢሆኑም ሴት ወንድ ተብሎ የሚለያየው ነገር የለም። ማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ልጅ አድጎ ሥራ ሰርቶ አግብቶ ወልዶ መኖርን ቢጠበቅም ያ አልሆነም ብሎ ግን ሀሜት ዓይነት ባህሪ አለመኖሩ ልዩነት አለው።

እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ሴት ልጆች በልጅነታቸው ቢያረግዙ አይደገፍም ስህተታቸውንም ለማስተካከል የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት አለመኖሩን ታነሳለች። አእምሮ ህሙማንን የሚሰበስብ የለም። ቤተሰባዊ ትስስር ቢኖርም አደባባይ ለሚወጡ ሰዎች ግን ከመጠቋቆም ባለፈ የመፍትሔ አካል ሲሆኑ አይታየም። ይህ ደግሞ እንደ ማህበረሰብ የሚያስተች በመሆኑ ቢስተካከል የሚል ሃሳብ ታነሳለች።

ሌላው ሴት በተፈጥሮዋ ከወንድ የምትበልጥበት፤ ከወንድ እኩል የማትሆንበት፤ እኩልም የምትሆንበት ሁኔታ አለ። ሴት ወንድ እኩል እንሁን በማለት ከመፎካከር ይልቅ ሁሉም የተለያየ ተፈጥሮ ባለቤት መሆኑን በመረዳት ለስኬት አብሮ መሥራት የተሻለ አማራጭ መሆን አለበት ትላለች።

«በሀገራችንም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገርመኝ ወንዶች ኩሽና አይገቡም ማለት ሴት መኪና አትነዳም ከማለት አይተናነስም።» የምትለው ሮማን ሰው ሰው በመሆኑ እኩል ነው በሚለው ሃሳብ በመግባባት ክርክርን መራቅ እንደሚገባ ትናገራለች።

ቀሪ ዘመናንም ለራሷንም ሆነ የሌሎችን ስኬት በሚያቀላጥፉ ተግባራት ላይ በመሰማራት ለማሳለፍ እንደምታስብ ነግራን የሞቀ ጨዋታችንን አብቅተናል። ቸር ይግጠመን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

እንደ ዓባይ ኹረት ፈሶ፤ እንደ ጣና ሐይቅም ተንጣሎ፤ ትናንትናን ከዛሬ አጋምዶ አዲስ ዘመን በትውስታዎቹ ያመላልሰናል። አንዴ ወደ ትናንት ደግሞም ወደዛሬ እየመለሰ የሕይወት ዘመን መስታየታችን ነው። ዓባይ አልነጠፈም፤ ጣናም አልደረቀም። የአዲስ ዘመን የትውስታ ገጸ በረከቶችም ተመዘው አያልቁም። ወጣ ብለን ከባሕር ማዶ አሻግረን እያስታወስን፤ በዓለማችን ዙሪያ ከተከወኑ አስገራሚ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል ጥቂቶቹን መራርጠን ልናካፍላችሁ ወደናል። ዝነኛው፤ የጡጫው ጌታ መሐመድ ዓሊ ቂሙን ለመበቀል ሲል መቶ ዛፎችን ቆራርጦ ፈልጧል... ከዛሬ አርባ ዓመታት በፊት አዛውንቱ በርከት ያሉ የእግር ኳስ ጨዋታ ውጤቶችን፤ ከጨዋታው በፊት በትክክል በመገመት 3 ሚሊዮን ብራቸውን ዝቀዋል... ነገሩ እንደዛሬው የቤቲንግ አጀብ ይሆን? ከወደ ጃካርታዋ ሲሊበስ ደግሞ በአይጦች ላይ የጦርነት ዘመቻ በመክፈት እያንዳንዱ ሰው 8 አይጦችን እንዲገድል ትዕዛዝ ተላልፏል። በአንድ ጀንበርም 2 ሚሊዮን ያህል አይጦችን ገድለዋል። ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ...ደብዳቤዎቹ ከነምላሾቻቸው ይጠብቁናል።

### ዓሊ ቂሙን ለመበቀል መቶ ዛፎች ፈልጧል

ባለፈው መጋቢት ወር አገጩ ወልቆ ሆስፒታል እስኪገባ ለብዙ ዓመት የያዘውን ክብር በኬን ኖርተን የተነጠቀው መሐመድ ዓሊ በድጋሚ ግጥሚያ በማሸነፍ ቂሙን ሊበቀል ችሏል።

.......

ዓሊ ይህ ውድድር የሕይወቱ ብርሃን መዳፈኛ መሆኑ ስለገባው መሞት ወይም መዳን የሚለውን ዓላማ ተከትሎ የተጋጠመ ስለሆነ በጨዋታው ላይ ያደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ በጣም ጥንቃቄ የተሞላበት እንደነበር ተገልጧል።

የ36 ዓመት ዕድሜ ያለው ዝነኛው ዓሊ ባለፈው መጋቢት ወር ሊሸነፍ የቻለው በመንደላቀቁና አለሁ አለሁ በማለቱ መሆኑ ስለገባው በአሁኑ ጊዜ የቀረበው ቂሙን ለመወጣት አፍ ሳያበዛ በምስጢር ጥንቃቄ የተሞላበት ልምምድ በማድረግ ነው።

ዓሊ የአሁኑ ልምምዱ ከ92 ኪሎ ወደ 86 ዝቅ ያደረገውን፤ ለክብደት ቅነሳና ጥንካሬ እንዲረዳው ከመቶ በላይ ዛፎችን የፈለጠና የቆረጠ መሆኑ ታውቋል።

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 16 ቀን 1965ዓ.ም )**

### በሲሊበስ 2 ሚሊዮን አይጦች ተገደሉ

ጃካርታ-በኢንዶኔሺያ ውስጥ በሲሊበስ ደቡባዊ ክፍል ተባዮችን ለማጥፋት በተደረገ ዘመቻ ሁለት ሚሊዮን አይጦች የተገደሉ መሆናቸውን የክፍሉ ባለሥልጣኖች ገለጡ።

እያንዳንዱ የሲድራፕ ቀበሌ ነዋሪ ቢያንስ ስምንት አይጦችን እንዲገድል በተሠጠው ትዕዛዝ መሠረት፤ ሕዝቡ ዘምቶ የተጠቀሱትን አይጦች ለማጥፋት ችሏል።

አይጦቹ የተገደሉበት ምክንያት 24 ቶን ያህል የሩዝ ምርት በማውደማቸው ነው።

**(አዲስ ዘመን መስከረም 13 ቀን 1966ዓ.ም)**

### አይጦችን ከቤት ለማባረር የሚመገቡትን ማሳጣት ነው

አይጦች ቤት ውስጥ እየገቡ በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለማድረግ አንዱ የመከላከያ ዘዴ፤ ምግብ እንዳያገኙ ማድረግ መሆኑን ፕሮፌሰር ሰር ዊሊያም ጃክሰን ገለጡ። አይጦች ወደ ሰዎች መኖሪያ ቤት የሚገቡት ለምግብ ፍለጋ ስለሆነ፤ ሰዎች ዕቃቸውን በሚገባ ከድነውና አይጦች እንዳይደርሱበት ካደረጉ አይጦቹ ሲራቡ ቤቱን ለቀው በመውጣት በውጪ ምግብ ፍለጋ ይሄዳሉ ብለዋል።

.......

ፕሮፌሰር ዊሊያም ጃክሰን ከኢትዮጵያ የእርሻ ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር አይጦች በሰብል ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለአንድ ወር ያህል በየጠቅላይ ግዛቱ ተዘዋውረው አጥንተዋል።

**(አዲስ ዘመን ታኅሣሥ 5 ቀን 1965ዓ.ም)**

### አዛውንቱ በስፖርት ትንቢት 3 ሚሊዮን ብር አገኙ

ሚስተር ዴቪድ ግሪፊት የተባሉ የ80 ዓመት አዛውንት በስፖርት ትንቢት 3 ሚሊዮን 525 ሺህ ብር ያገኙ መሆኑን ሬውተር ከለንደን አስተላለፈ።

ለቅድማያትነት የበቁት ሚስተር ግሪፊት ከውድድሩ በፊት የስምንት የእንግሊዝ ሻምፒዮን ያለፈውን ቅዳሜ ውጤት በቅድሚያ በትክክል ስለተነበዩ ይኸው ገንዘብ ወዲያው በቼክ እንዲከፈላቸው ተደርጓል።

አዛውንቱም ገንዘባቸውን እጃቸው ካደረጉ በኋላ፤ ይህን ሁሉ ገንዘብ እንድበላ የሚያደርገኝን ዕድሜ ፈጣሪ እንደሚሰጠኝ ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል።

**(አዲስ ዘመን ጥር 9 ቀን 1965ዓ.ም)**

### ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ

*ወይዘሮ ንጋትዋ ከበደ ስለ ወንደ ላጤዎች የቤት ንጽሕና ጉድለት የጻፉቸውን አንብቤያለሁ። ለመሆኑ ወይዘሮዋ ለምን ወንደላጤዎች ቤት ሔደች?

አብርሃም አሉማ

-ሌላውጋማ በሩ ዝግ ነው።

**(አዲስ ዘመን ታኅሣሥ 14 ቀን 1965ዓ.ም)**

*አፖሎ 15 ጨረቃ ላይ ባረፈችበት ሌሊት አንድ ልጅ ተወለደልኝ። አሁን ደግሞ አፖሎ 17 በመጠቀችበት ሌሊት ሌላ አንድ ልጅ አግኝቻለሁ። ያቺኛዋን ስምዋን ጨረቃ ብያታለሁ። ለዚህችኛዋ የሚስማማትን ስም አንተ አውጣልኝ?

መሐመድ ይማም

ከጅማ

-ይሄ የአየሩ ጉዳይ ተስማምቶሃል ማለት ነው። ጸሐይ ብትላትስ? ያለዚያም ኮከቤ በላት። ግን በአላህ ይገዘሃለሁ አፖሎ እንዳትላት።

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 10 ቀን 1965ዓ.ም)**

*እስከዛሬ ድረስ እኔ የማጠናው ማታ ማታ ጫት እየቃምኩ ነው። ግን ከዚህ የተሻለ የአጠናን ዘዴ እንዳለህ ንገረኝ ምክንያቱም ዘንድሮ የአሥራ ሁለተኛን ክፍል መልቀቂያ ፈታና ስለምወስድ ነው።

-ኋላ ሱስ ሆኖብህ እንዳትቸገር ተጠንቀቅ። ለጥናቱ ማታ ጥሩ ነው። ቀን ሙቀቱ አያስጠናህም።

**(አዲስ ዘመን ኅዳር 23 ቀን 1965ዓ.ም)**

*ከዚህ በፊት የጡት ማሳደጊያ አለ ብለህ ነበር። እኔ ደግሞ ጡቴን ለመቀነስ ስለምፈልግ እባክህ መቀነሻ ያለበትን ንገረኝ?

በዛብሽ በቀለ

---

መቀነሻው የት እንደሚገኝ አላውቅም። እንደኔ እንደኔ ባትቀንሽው መልካም ይመስለኛል። ከሴት ልጅ መልክ አንዱ ጡት ነው። የሌላቸው ተቸግረው በጡት መያዣ አሳድገውት ሲሔዱ አንቺ ልቀንስ ማለቱን ትተሽ «ደህና ጡት የሰጠከኝ አምላክ ተመስገን» እያልሽ ኑሪ።

**(አዲስ ዘመን ሰኔ 10 ቀን 1965ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ



## ሳውዲ ዐረቢያ አዲስ ድፍድፍ ነዳጅ አገኘች

ሀገሪቱ በአምስት ስፍራዎች አዳዲስ የነዳጅ ሀብት ማግኘቷን አስታውቃለች፡፡ የዓለማችን ቀዳሚ ነዳጅ ላኪ ሀገር የሆነችው ሳውዲ ዐረቢያ ተጨማሪ የነዳጅ ሀብት ማግኘቷ ተገልጿል፡፡ የሀገሪቱ ዜና አገልግሎት እንዳስታወቀው በምሥራቃዊ ሳውዲ አምስት አዲስ የነዳጅ ሀብት አግኝታለች፡፡

የሳውዲ መንግሥታዊ የነዳጅ ኩባንያ የሆነው አርማኮ ሁለት የነዳጅ ማውጫ ስፍራዎችን እንዳገኘ የሀገሪቱ ኢነርጂ ሚኒስትር ልዑል አብዱላዚዝ ቢን ሳልማን ተናገረዋል፡፡ በምሥራቃዊ ሳውዲ ዐረቢያ የተገኙት እነዚህ የነዳጅ ማውጫ አካባቢዎች በቀን በሚሊዮን የሚቆጠር በርሜል ነዳጅ ማምረት ያስችላሉ ተብሏል፡፡

አሁን ላይ ተገኙ የተባሉት የነዳጅ ሀብት ስፍራዎች ከዚህ በፊት ፍንጭ ተገኝቶባቸው ተጨማሪ ክትትል ሲደረግባቸው እንደቆየ ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡ ሳውዲ ዐረቢያ አሁን ላይ በቀን 12 ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ በማምረት ላይ ስትሆን የዓለማችን ቁጥር አንድ ነዳጅ ላኪም ሀገር ናት፡፡

አሜሪካ ከ2018 ጀምሮ የዓለማችን ቀዳሚዋ ነዳጅ አምራች ሀገር ስትሆን በ2022 ላይ ብቻ በየቀኑ በአማካኝ 18 ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ አምርታለች፡፡ ቬንዙዌላ፣ ሳውዲ ዐረቢያ፣ ካናዳ፣ ኢራን እና ኢራቅ በቅደም ተከተላቸው የዓለማችን አምስት ነዳጅ ሀብታም ሀገራት ሲሆኑ ሳውዲ ዐረቢያ በ2022 ዓመት ብቻ 311 ቢሊዮን ዶላር ከነዳጅ ሽያጭ ገቢ ማግኘቷ ተገልጿል፡፡

ኢትዮጵያ የነዳጅ ሀብት ካላቸው የዓለማችን ሀገራት መካከል አንዷ ስትሆን 428 ሺህ በርሜል ነዳጅ ሀብት በመያዝ 98ኛዋ ሀገር መባሏን አል ዐይን ዘግቧል፡፡



## ለአየር ንብረት ጥበቃ ሥራዎች 24 ትሪሊዮን ዶላር ያስፈልጋል

የአየር ንብረት ጥበቃ ሥራዎችን በፍጥነት ለማነቃቃት በማደግ ላይ ለሚገኙ እና ድሃ ሀገራት በጥቂቱ ሁለት ነጥብ አራት ትሪሊዮን ዶላር ፈንድ ማድረግ እንደሚገባ ተገለጸ።

ለ30 ዓመታት በዓለምአቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የሠሩት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ማህሙድ ሞሄልዲን እንደገለጹት፥ የዓለም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ በሁሉም ዘርፎች የፋይናንስ አቅርቦቱ በእጥፍ ሊያድግ ይገባል። የአየር ንብረት ለውጥን ለሚገቱ ሥራዎች ለታዳጊ ሀገራት የሚቀርበው ፋይናንስ ሁለት ነጥብ 4 አራት ትሪሊዮን ዶላር መድረስ እንዳለበትም አሳስበዋል።

ከዚህ ውስጥ አንድ ትሪሊዮን ዶላሩ በዓለም አቀፍ የልማትና የፋይናንስ ተቋማት በኩል መቅረብ እንዳለበት በመጥቀስ። ዶክተር ሞሄልዲን ለኤምሬትሱ የዜና ወኪል ዋም እንደተናገሩት፥ በዱባይ በሚካሄደው የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ የፋይናንስ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል።

የመንግሥታቱ ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (ኮፕ27) ባለፈው ዓመት በግብጽ ሲካሄድ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳት እና ኪሳራን የሚያካክስ ድጋፍ እንዲደረግ መስማማታቸው ይታወሳል። ሀገራት ስለሚደረገው ድጋፍ የሚደራደርና 28 አባላት ያሉት ኮሚቴ ማዋቀራቸውም አይዘነጋም።

ይህ ኮሚቴ ለአንድ ዓመት በአቡዳቢ ሲያደርገው የነበረውን ድርድር ያጠናቀቀ ሲሆን፥ ጊዜያዊ ስምምነት ላይ ደርሷል። ይሄው ጊዜያዊ ስምምነት በኮፕ28 ጉባኤ ለመሪዎች ቀርቦ ንግግር እንደሚደረግበት ዶክተር ሞሄልዲን ገልጸዋል።

ዶክተር ማህሙድ ሞሄልዲን በግብጽ ለአየር ንብረት ለውጥ መከላከል የሚውል የፋይናንስ አቅርቦትን በማመቻቸት እና በሌሎች ተያያዥ ሥራዎች አርአያ የሚሆን ተግባር በመፈጸም በመንግሥታቱ ድርጅት እውቅና የተሰጣቸው መሆኑን አል ዐይን ዘግቧል።

በሰው ልጅ ድርጊት ምክንያት የምድራችን ሙቀት መጠን ከቀን ቀን እየጨመረ ነው። የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ ደግሞ የእያንዳንችንን ሕይወት እየቀየረው ይገኛል። በየቦታው ድርቅ እየታየ ነው፤ የውቅያኖሶች መጠን ጨምሯል፤ በርካታ ነፍሳት ከምድራችን እየጠፉ ነው። ከፊት ለፊታችን ያለው ፈተና ከባድ ቢሆንም መፍትሔዎች አሉ። ከእነዚህ መፍትሔዎች መካከል የደን ሽፋንን ማሳደግ፣ ከኢንዱስትሪዎች የሚለቀቀውን በካይ ጋዝ መቀነስና መሰል ርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ደግሞ አስፈላጊው ፋይንናንስ መድቦ መሥራት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## 1ኛ፤2ኛ፤3ኛ፤... ሳተላይት

ኢትዮጵያ ETRSS-02 የሚል ስያሜ የተሰጣትን ሦስተኛዋን የመሬት ምልከታ ሳተላይት በሁለት ዓመታት ውስጥ ለማምጠቅ በዝግጅት ላይ መሆኗን የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት በዚያ ሰሞን ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ)ገልጿል፤ ከዚህ በፊት ወደ ሕዋ የመጠቁት ሳተላይቶች የተቀመጠላቸውን የአገልግሎት ጊዜ በመጨረስ ተልዕኳቸውን በስኬት አጠናቀዋል።

የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አብዲሳ ይልማ፤ ሦስተኛውን ሳተላይት መምጠቅን በተመለከተ መንግሥት የፋይናንስና የኢኮኖሚ አዋጪነት ጥናት ማድረጉን፤ ጥናቱ ከዚህ በፊት ወደ ሕዋ ከመጠቁት ሳተላይቶች ተሞክሮ በመውሰድ የቀጣዩን ሳተላይት መረጃ ከመጠቀም አልፎ ሌሎች ተልዕኮዎችን በግልጽ ማስቀመጡንም አስረድተዋል።

የሳተላይቱን ጨረታ የተመለከተ መረጃ የመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት ውስጥ እንዲገባ መደረጉንና በቀጣይ ወራት ዓለም አቀፍ ጨረታ እንደሚወጣ ጠቁመው፤ በታኅሣሥ 2012 ዓ.ም ኢትዮጵያ በታሪኳ የመጀመሪያውን ETRSS-01 የመሬት ምልከታ ሳተላይት ከቻይና የሳተላይት ማስወንጨፊያ ጣቢያ ወደ ሕዋ መላኳን ያወሳሉ። በታኅሣሥ 2013 ዓ.ም ደግሞ ET-Smart-RSS የተሰኘችውን ሁለተኛዋን የመሬት ምልከታ ሳተላይት በተመሳሳይ ከቻይና ወደ ሕዋ አምጥቃለች።

የመጀመሪያዋ የመሬት ምልከታ ሳተላይት በሕዋ ከሁለት ዓመት ከግማሽ እስከ ሦስት ዓመት እንዲሁም ሁለተኛው ሳተላይት ደግሞ ቢያንስ ለአንድ ዓመት እንደምትቆይ በወቅቱ ተገልጾ ነበር። በዚሁ መሠረት ሁለቱ ሳተላይቶች በተቀመጠላቸው ጊዜ የአገልግሎት ጊዜያቸውን አጠናቀው የተሰጣቸውን ተልዕኮ ማሳካታቸውን፤ ETRSS-01 የተሰኘችው ሳተላይት ከተቀመጠላት ጊዜ በላይ ተጨማሪ ዘጠኝ ወራት አገልግሎት መስጠቷን፤ በቀጣይ ሳተላይቶቹን ከአጋር አካላት ጋር በመሆን የማስወገድ ሥራ እንደሚከናወንም የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ገልጸዋል።

ለETRSS-01 ሳተላይት 8 ሚሊዮን ዶላር እና ለ ET-Smart-RSS ሳተላይት 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ወጪ እንደተደረገባቸውም ፤ ከሳተላይቶቹ የተገኙት መረጃዎች ለግብርና፣ ቱሪዝም፣ መሬት አስተዳደር፣ ተፈጥሮ ሀብት፣ ለአደጋ ስጋት ቅነሳና ሌሎች ሥራዎች በግብአትነት መዋላቸውን፤ ተቋማትም የወሰዷቸውን መረጃዎች ጥናትና ምርምርን ጨምሮ ለተለያዩ ሥራዎቻቸው እየተጠቀሙበት እንደሚገኝ፤ ከሳተላይት ጥራት ያለው መረጃ መቀበል የሚያስችል የብዝሃ ሳተላይት መረጃ መቀበያና መቆጣጠሪያ ጣቢያም በ2015 ዓ.ም ወደ ሥራ መግባቱን፤ ኢትዮጵያ ሳተላይት ማምጠቅን ጨምሮ ሌሎች የስፔስ ሳይንስ ሥራዎች ማከናወን የጀመረችው በቅርብ ዓመታት ውስጥ እንደሆነና ከዚህም አንጻር እየተገኙ ያሉ ውጤት መልካም የሚባሉ መሆናቸውን ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

ሳተላይቶች ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለግብርና እና ለከተሞች ልማት እንዲሁም ለሌሎች ተቋማት ሥራ ጠቃሚ የሆኑ የተለያዩ ምስሎችን ልከዋል። ኢትዮጵያ የራሷን ሳተላይት ከማምጠቋ በፊት እነዚህን መረጃዎች ሳተላይት አምጥቀው ፎቶ ከሚያስነሱ ሀገሮች በመግዛት ትጠቀም ነበር። በዚህም ሳቢያ የሳተላይት መረጃውን ለመግዛትም በዓመት 250 ሚሊዮን ብር ስታወጣ የቆየች ሲሆን ይህም ከዓመት ዓመት ይጨምር እንደነበር የዘርፉ ባለሙያዎች ከዓመታት በፊት የተሠራ ጥናትን በመጥቀስ ይናገራሉ።

> **የታሪክ አባት በመባል የሚታወቀው ሔሮዶቶስ ኢትዮጵያውያንን 'ከሰሐራ በታች የሚኖሩ፣ ጥቁር ቆዳ ያላቸው ... ብልሆች፣ በዓላቶቻቸውና ሀሴታቸውም ሳይቀር አማልክትን ስለሚያስደስት የአማልክት አምላክ እየሄደ በዓላቱን በደስታ አብሯቸው ያሳልፋል ' ብሏል**

አፍሪካ ውስጥ ካሉ ሀገራት በሕዋ ጥናት ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ አልጄሪያ እና ግብፅ ጥሩ ስም መገንባት የቻሉ ሲሆን ኢትዮጵያ ግን ከእነርሱ አንጻር ገና ጀማሪ ናት።

የሕዋ ጥናት በዓለም ላይ በፍጥነት እየዘመኑ ካሉ ዘርፎች መካከል ይጠቀሳል። የሰው ልጅ ስለሚኖርባት ምድር ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ካለው ፍላጎት ባሻገር ሕዋን አብጠርጥሮ ለማወቅ ጥረት እያደረገ ነው። ለዚህ ደግሞ ሳተላይቶች ዋነኛ መሣሪያዎቹ ናቸው። ከህዋ ላይ በመሆን መሬትን ማሰስ የመሬት ምልከታ ሳተላይት ተግባር ነው። ሳተላይቱ መረጃ ሲሰበስብ ይህ ቀረህ አይባለውም። ከግዙፍ ክንውኖች እስከ ጥቃቅን እንቅስቃሴዎች ይመዘግባል።

እንደ ባለሙያዎች አባባል ሳተላይቱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው። የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር፣ የተፈጥሮ አደጋዎች ከመድረሳቸው በፊት አስቀድሞ ለመተንበይ፣ ደኅንነትን ለመጠበቅ እና ለሌላም ይውላል። የአየር ንብረት ለውጥ የመላው ዓለም ስጋት በሆነበት በዚህ ዘመን፤ አንዳች ተፈጥሯዊ አደጋ ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ መረጃ ማግኘት የበርካቶችን ሕይወት ለመታደግ ያስችላል።

ለአብነትም በአንድ አካባቢ ያሉ የዛፎችን ቁጥር፣ የአየርንብረት ለውጥ እና ሌሎች መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ እንደ ጎርፍ ያሉ አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት መተንበይ የሚቻልበት ዕድል አለ። ግብርና ቀዳሚ መተዳደሪያ በሆነባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት የቱ አካባቢ ምርታማ ነው? የአየር ንብረት ለውጥ ሊኖር ይችላል? የሚሉ ጥያቄዎች በቀላሉ ለመመለስ የሳተላይት መረጃ አስተማማኝ እና አስፈላጊ ነው።

አንድ የግብርና አካባቢን የሚያሳይ የሳተላይት ፎቶግራፍ ስለ እርሻ መሬቱ፣ ስለ ውሃው፣ ስለ አፈሩ ዝርዝር መረጃ ይሰጣል። መረጃዎቹን በመጠቀም ምርታማ የሆኑ አካባቢዎችን መለየት እና የሚገኘውን የምርት መጠን በትክክል ማወቅም ይቻላል። በተጨማሪም ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ ፋብሪካዎች የት መገንባት አለባቸው? ለሚለው ጥያቄ ከሳተላይት የሚገኙ መረጃዎች ጠቃሚ ናቸው።

ሳተላይት ማምጠቅ ብዙ ትርጉም እንዳለውና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ያደጉ ሀገራት የዕድገት ምስጢርም መነሻው ይህ ነው። ይህ ጅምር ለኢትዮጵያ ዕድገት ትልቅ ትርጉም አለው ይላሉ የዘርፉ ልሒቃን። በዜጎችና ምሁራን ዘንድም አዲስ ነገር ለመፍጠር ትልቅ መነሳሳት ይሆናል። የምትመጥቀው ሳተላይቷ ለከተማ እና ገጠር መሬት አስተዳደር፣ ማኅበራዊ ጉዳዮች፣ ሕዝብ አሰፋፈር፣ ምርጫና ሕዝብ ቆጠራ፣ ለማኅበረሰብ ልማቶችና ተያያዥ ጉዳዮች መረጃ ለመሰብሰብ ትልቅ ድርሻ ይኖራታል። በድንበር አካባቢ የሚስተዋሉ ተላላፊ ወንጀሎች፣ ሕገ ወጥ የመሣሪያ ዝውውርና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመከላከል በሀገሪቱ የሚከናወኑ ታላላቅ የልማት አውታሮችን ለመጠበቅና ከጥቃት ለመከላከልም አበርክቶዋ የጎላ ነው።

ማዕድናት፣ መሬት፣ ውሃና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም፣ የገጠርና የከተማ መሬት አያያዝና አጠቃቀምና ፍትሃዊ አሠራርን መሠረት ለማስያዝ ብሎም አዳዲስ ፖሊሲዎችን ለማርቀቅም ከሳተላይት የሚገኘው መረጃ የላቀ ሚና አለው። እንደ ዘርፉ ምሁራን ገለፃ፤ አሁን ባለው ጅምር ኢትዮጵያ በስፔስ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ በቀላሉ ትገባለች።

ይህም በዓለም አቀፍ ሕግ ላይ የመወሰንና የመደራደር ሚና ይኖራታል። ኢትዮጵያ የሌሎች ሀገራት መረጃ ስለሚኖራት በመተባበርና በመከባበር እንድትሠራ ያግዛታል። ሉዓላዊ ሀገራትን መብት እንዳይጣስም ሌሎች ሀገራትም በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡ ከማገዙ ባሻገር የመደራደር አቅም ስለሚፈጥርላት ተሰሚነቷ ይጨምራል።

ይሁንና ሀገራችን ከ3 እና 4ሺህ ዓመታት በፊት በህዋ ምርምር ዘርፍ የዛሬዎቹን ልዕለ ኃያላን ከፊት ሆና ስትመራ እንደነበር የጥንት ብራና መጽሐፍትና ስንክ ሳሮች ዋቢ ከመሆናቸው ባሻገር ዓለምአቀፉ የአስትሮኖሚ ኅብረት በሀገራችን ልዕልት፣ ንግሥትና ንጉሥ ስም ሕብረ ከዋክብት constellations መሰየሙን ስንቶቻችን ይሆን የምናውቀው!? ስለ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የሥነ – ፈለክ (የሕዋ) እውቀትና በዘመን አቆጣጠር ምን ያህል የተራቀቁ እንደነበሩ በማስረጃ የሚተነትነው የሮዳስ ታደሰና ጌትነት ፈለቀ (ሁሉም ፒ ኤች ዲ ሠርተዋል)።

በጋራ በደረሱቱ ፤ «አንድሮሜዳ» መጽሐፍ 5ኛ ዕትም ላይ ፤«... ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ያሉ የውጭው ዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ...' ጥንታዊ ዘር ' በመባል የምትታወቀውን ኢትዮጵያን ... አውሮፓና እስያ ባልሠለጠኑበት ዘመን ... ፍልስፍና፣ ሥነ ጽሑፍ ፣ ሒሳብ ፣ ግብርና፣ ሕክምና፣ የከዋክብት ጥናት ...የኢትዮጵያውያን ነባር ሀገር በቀል እውቀቶች እንደነበሩ ተናግረዋል:... » ይህ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለሥነ ፈለክ የማይናወጥ መሠረት እንደነበራቸው ያረጋግጣል::

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ ባለቤት መሆኗን እና ለሥነ – ፈለክ ምርምር ወረት፣ መነሻ እንደነበራት የሚያረጋግጡ የቀደምት ሊቃውንት እማኝነት ከፍ ሲል በተገለፀው መጽሐፍ እንደሚከተለው ተዘግቧል:: «60 ዓመት ቅድመ ልደት ክርስቶስ የነበረው ዲዎዶርስ ሴኩለስ የተባለ የታሪክ ሊቅ ' አውሮፓውያን ኋላ ቀር እድገት አኗኗር ላይ በነበሩበት ወቅት ኢትዮጵያ ታላቅ ሥልጣኔ ላይ የነበረች ...ኢትዮጵያውያን ለግብጻውያን ሥልጣኔ ያስጀመሩና እስከ ሕንድ ድረስ የገዙ ናቸው::

' ... በ700 ዓ.ም የነበረው የቤዛንታይኑ እስቲፋንስ ባካሄደው ጥልቅ ጥናት ' ኢትዮጵያ መሬታችን ላይ የተመሰረተች የመጀመሪያ ሀገር ናት ' ሲል አርኖልድ ኸርማን ሉድዊግ የተባለ የጀርመናዊ የታሪክ ፀሐፊ ደግሞ ' ኢትዮጵያን የመሰለ ጥንታዊ ሀገር ወዴት ይገኛል!? ' ሲል ይሞግታል ... ከ800 ዓመት ክርስቶስ ልደት በፊት የኖረው ሆሜር ኢሊያድና እና ኦዲሴይ በተባሉ ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎቹ ኢትዮጵያውያን ' እስከ መሬት ጫፍ ድረስ የሚኖሩና ከአምላክ ጋር ቅርበት ያላቸው ' በማለት ይገልጻቸዋል::

የታሪክ አባት በመባል የሚታወቀው ሔሮዶቶስ ኢትዮጵያውያንን 'ከሰሐራ በታች የሚኖሩ፣ ጥቁር ቆዳ ያላቸው ...ብልሆች፣ በዓላቶቻቸውና ሀሴታቸውም ሳይቀር አማልክትን ስለሚያስደስት የአማልክት አምላክ እየሄደ በዓላቱን በደስታ አብሯቸው ያሳልፋል ' ብሏል:: ...ዲዮዶር የተባለ የሮም ፀሐፊ ደግሞ 'ከግብፅ በፊት ሥልጡንና ገናና ነበረች:: ግብፅን ቀኝ ገዝታ 18 የኢትዮጵያ ነገሥታት ተፈራርቀውባታል:: ...' ይላል::

«መጽሐፉ ሀገራችን የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት መሆኗን በአደባባይ ካስመሰከረ በኋላ በዓለምአቀፉ የአስትሮኖሚ ሕብረት የተሰጣትን ቦታ ይተነትናል :: "...ሕብረ ከዋክብት constellations ማለት በሰማይ ላይ የሆነ ዓይነት ቅርፅ የሚሠራ የከዋክብት ስብስብ ሲሆን ቅርጹም ከማይቶሎጂ ጋር በተያያዘ መልኩ የሰው፣ የእንስሳት ወይም ሕይወት የሌለው ነገር ሆኖ ሊገለጽ ይችላል::...ዓለምአቀፉ የአስትሮኖሚ ሕብረት በ1930 ዓ.ም ከ88 ሕብራተ ከዋክብት ውስጥ ሦስቱን ማለትም አንድሮሜዳን ፣ ካሲዮፒያንና ሴፌውስን በኢትዮጵያውያን ስም መዝግቧል:: ... አንድሮሜዳ የኢትዮጵያ ልዕልት ስትሆን ፤ ካሲዮፒያን ደግሞ የኢትዮጵያ ንግሥት ናት:: ሴፌውስ ደግሞ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነው :: ...»

ለሥነ ፈለክ አርፋጅም ፣ ኮራጅም አይደለንም:: አልፋ ነን:: ለ4 ሺህ ዓመታት ተዳፍኖ የነበርን ፍም በETRSS – 1 ሳታላይት እፍ ብለን አፈገግነው እንጂ:: ከፍ ብለን እንደተመለከትነው በህዋ ጥበብ ፣ እውቀት ከበኩራን ተርታ ተሰላፊ ነበርን:: ለእልፍ አእላፍ ዓመታት የተጠናወተን አፍርሶ ከዜሮ የመጀመር አባዜ ብኩርናችንን ቢያስነጥቀንም:: የአክሱም ሐውልት ፣ የላሊበላ ወቅር አብያተ ክርስቲያናት ፣ የፋሲል ግንብ ፣ የጥያ ትክል ድንጋዮች ሳያፈርሱ እንዴት እንዳቆዩን ይገርመኛል:: ከሦስት አመት በፊት ወደ መጠቀችው ሳታላይት ስንመለስ ከዚያ ባለ ብዙ ገድላት የእነ ሴፌውስ ትውልድ ጋር ድልድይ ሆና እንደገና ታገናኘለች:: መንኮራኮር ሆናም በምናብ በምልሰት flash back 4ሺህ ዓመት ወደ ኋላ ትወስደናለች::

**ሻሎም ! አሜን ::**

# ስፖርት

## የሉሲዎቹ ተተኪዎች በወሳኝ የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ምዕራፍ

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ሴቶች ብሔራዊ ቡድን ታሪክ ለመሥራት ተቃርቧል:: እ.አ.አ በ2024 በኮሎምቢያ አስተናጋጅነት በሚካሄደው 11ኛው የፊፋ የሴቶች ከ20 ዓመት በታች የዓለም ዋንጫ የአፍሪካ ዞን የማጣሪያ ጨዋታቸውን እያደረጉ የሚገኙት የሉሲዎቹ ተተኪዎች የማሊ አቻቸውን በደርሶ መልስ ጨዋታ 6 ለምንም ማሸነፍ ችለዋል::

የሉሲዎቹ ተተኪዎች ባሳለፍነው ቅዳሜ ኅዳር 1/2016 ከሜዳቸው ውጪ ባማኮ ላይ ባደረጉት ጨዋታ ንግሥት በቀለ በ57ኛው ደቂቃ እና እሙሽ ዳንኤል በ68ኛው ደቂቃ ባስቆጠሯቸው ሁለት ጎሎች 2 ለ 0 ማሸነፉ የሚታወስ ነው። ከትናንት በስቲያ ደግሞ የመልሱን ጨዋታ በአዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስቴድየም አከናውነው 4ለ0 በሆነ ውጤት ማሸነፍ ችለዋል:: በጨዋታው የሉሲዎቹ ተተኪዎች በመጀመሪያው አጋማሽ በ35ኛውና በ45ኛው ደቂቃ በእሙሽ ዳንኤል አማካኝነት በተቆጠሩ ሁለት ጎሎች እየመራ ለእረፍት ወጥቷል። ከእረፍት መልስም ለኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ሴት ብሔራዊ ቡድን መዓድን ሳህሉ በ66ኛው ደቂቃ እንዲሁም መሳይ ተመስገን በ69ኛው ደቂቃ ጎሎችን አስቆጥረው በፍፁም የበላይነት ማሸነፍ ችለዋል::

በሁለቱ የደርሶ መልስ ጨዋታዎች ለኢትዮጵያ ቡድን ልዩነት ፈጣሪ የሆነችው አጥቂዋ እሙሽ ዳንዔል ከስፖርት ቤተሰቡ ሙገሳን አግኝታለች:: ከሐዋሳ ወጣት ቡድን የተገኘችው እሙሽ ለኢትዮጵያ ከ17 እና ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድኖች ተሰልፋ በመጫወት ባለፉት አራት ዓመታት ለሀገሯ በርካታ ጎሎችን ማስቆጠር ችላለች:: ለኢትዮጵያ በተለያዩ የዕድሜ እርከን ለሚገኙ ብሔራዊ ቡድኖች በአፍሪካ እና ዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች በርካታ ጎሎችን እያስቆጠረች የምትገኘው እሙሽ ማሊ ላይ በሁለት ጨዋታ ሦስት ግብ ያስቆጠረች ሲሆን በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ያስቆጠረቻቸውን ግቦች ወደ 13 ከፍ አድርጋለች::

በአሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል የሚመራው ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን ማሊን በድምር ውጤት 6 ለ 0 ማሸነፉን ተከትሎ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ዋንጫ ለመሳተፍ የ180 ደቂቃ ፍልሚያ ብቻ ቀርቶታል:: በመጨረሻው ዙር ማጣሪያ የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ከሞሮኮ ጋር ጥር 3 ቀን 2016 የሚያከናውኑም ይሆናል። ሞሮኮን በደርሶ መልስ ጨዋታ ካሸነፉም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኮሎምቢያ በሚካሄደው ከ20 ዓመት በታች የዓለም ዋንጫ ማለፋቸውን ያረጋግጣሉ።

ብሔራዊ ቡድኑ በዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ወደ መጨረሻው ዙር ማለፉን ካረጋገጠ በኋላ የቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል በሰጡት አስተያየት፣ «የዛሬውን ጨዋታ ብዙ ትኩረት አድርገንበት ነው የመጣነው። ከሜዳ ውጪ አሸንፈን ብንመጣም በሜዳችን ጥሩ መሥራት እንዳለብን ተነጋግረን ከተጫዋቾቻችን ጋር ብዙ ሥራዎችን ስንሠራ ነበር። ሙሉ ለሙሉ ተሳክቷል ብዬ አስባለሁ።» ብለዋል::

ስለ ቀጣይ ተጋጣሚያቸው ሞሮኮ ሲናገሩም «ሞሮኮ ጠንካራ ቡድን እንደሆነ እናውቃለን። የሞሮኮን ጠንካራ እና ደካማ ጎንም ለማወቅ እንደ ሀገር ትኩረት ሰጥተን መሥራት ይጠበቅብናል። ከዚህ በፊት እንደምንዘጋጀው ለቀጣዩ ጨዋታም ተገቢውን ዝግጅት በትኩረት እናደርጋለን።» በማለት ተናግረዋል::

በኮሎምቢያ አስተናጋጅነት በሚካሄደው የዓለም ከ20 ዓመት በታች የዓለም ዋንጫ 16 ሀገራት የሚካፈሉ ሲሆን ከኮሎምቢያ ውጪ ያሉትን ቀሪ 15 ተሳታፊ ሀገራት ለመለየት በስድስት አህጉራት የማጣሪያ ውድድሮች ይካሄዳሉ። አፍሪካ በዓለም ዋንጫው ሁለት ሀገራት የማሳተፍ ኮታ እንዳላት የዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር(ፊፋ) አስታውቋል። በውድድሩ የአፍሪካ ዞን ማጣሪያ 35 የአፍሪካ ሀገራት እየተሳተፉ ነው። የፊፋ ከ20 ዓመት በታች የሴቶች ዓለም ዋንጫ የአፍሪካ ዞን ማጣሪያ በአራት ዙሮች እንደሚከናወን የአፍሪካ የእግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን(ካፍ) አስታውቋል።



**የሴቶች ከ20 ዓመት በታች ብሔራዊ ቡድን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ዋንጫ ለመሳተፍ የ180 ደቂቃ ፍልሚያ ብቻ ቀርቶታል**